# ሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን


<u>አዘጋጅ</u>

**ሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ



<u>አሳታሚ</u>

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ

**ማኅበረ ቅዱሳን**

አዲስ አበባ

1996 ዓ.ም



www.eotc-mkidusan.org

© ማኅበረ ቅዱሳን
1996 ዓ.ም.

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

ይህ መጽሐፍ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
በማኅበረ ቅዱሳን
የኢዲቶሪያል ቦርድ ታርሞና ተስተካክሎ
የተፈቀደ ነው።

**አድራሻ**

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ
በሰ/ት/ቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን፣ ኅትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል

ፖ.ሳ.ቁ. ፩፬፬፻፸፰
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ስልክ 55 63 28/27

Email- eoc-m-kidusan@telecom.net.et



«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነስቷአል፡፡ ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ በክርስቶስ ደግሞ ህያዋን ይሆናሉና፡፡»1ኛቆሮ.15.20-21



«እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፣ ብርቱ የሆነ በእርሱ ለእኔ ታላቅ ሥራን አድርጓልና፡፡» ሉቃ. 1.49

# መታሰቢያ ነቱ



«በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ወጣቱን ትውልድ ለአንድ ዓላማ በማሰለፍና በሃይማኖታዊ አኗኗር በመቅረጽ የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕን ያህል የተሳካለት ሰው ያለ አይመስልም። ከዕለተ ዕረፍታቸው 10 ዓመታት በኋላ እንኳን የጻፏቸው መጻሕፍት፣ ያዘጋጇቸው የጽሑፍ ስብከቶችና በቃል ያስተላለፏቸው ትምህርቶች ለእያሌ ሰንበት ት/ቤቶች፣ የካህናትና የመምህራን ማሠልጠኛዎች ማስተማርያና የተግባር መመሪያ ሆነዋል።»

*ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ፣ ነሐሴ 1994 ዓ.ም.*

ይህ መጽሐፍ ወጣቱን ትውልድ በነገረ ሃይማኖት ዕውቀትና በመንፈሳዊ ሕይወት ለመቅረጽ፣ ትውልዱ የቤተ ክርስቲያን ፍቅር እንዲኖረው ለማድረግ ለተጉት፣ ዛሬ ላለው ኦርቶዶክሳዊ የስብከት ዘዴ ፋና ወጊ ለሆኑት፣ ዘመኑን የሚዋጁ የትምህርተ ሃይማኖትና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መጻሕፍትን ላዘጋጁት፣ ቤተ ክርስቲያን በዓለም መድረክ ተገቢ ቦታዋን እንድታገኝ ለተጋደሉት፣ የዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳምና የካህናት ማሠልጠኛ መሥራች ለሆኑት፣ ለ21ኛው መ/ክ/ዘ «ከሣቴ ብርሃን» ለብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ (1932-1982 ዓ.ም.) መታሰቢያ ይሁን።

*ጸሎታቸውና በረከታቸው በሁላችን ላይ ይደር፤ አሜን።*

www.eotc-mkidusan.org

# መግቢያ

«የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ» 2ኛጢሞ.3÷14 ከሚባሉት ውስጥ መጻሕፍተ ሊቃውንት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ሊቃውንት በየዘመናቸው የዘመኑን ጥያቄ ሊመልሱ የሚችሉ መጻሕፍትን አዘጋጅተዋል፡፡ በተለይም ከመናፍቃን መነሣት በኋላ ያሉት በየዘመናቸው ለተነሡት ጥያቄዎች ሁሉ መልስ የሚሆኑና የምእመናን ልቡና በኑፋቄ ማዕበል እንዳይናወጽ የሚያደርጉትን ምሥጢራት በፈርጅ እየተነተኑ ጽፈዋል፡፡ እነዚህም እንደ አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት፣ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፣ ነገረ ማርያምና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

እነዚህን መጻሕፍት ሲጽፉ ወይንም ምሥጢራት እያሉ ሲያዘጋጁም ከራሳቸው አንቅተው አይደለም፡፡ መሠረቱ የጌታችንና እርሱ አድሮባቸው ቀድመው ትንቢት የተናገሩ የነቢያት በኋላም ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የተረጐሙና ያስተማሩ የሐዋርያት ትምህርት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ አልተንቀሳቀሱም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ «መሠረትን ደግመን አንመሥርት÷ እርሱም ከሞተ ሥራ ንስሐና በእግዚአብሔር እምነት÷ ስለ ጥምቀቶችና እጆችንም ስለመጫን ስለ ሙታንም ትንሣኤ ስለ ዘላለም ፍርድም ትምህርት ነው፡፡» ዕብ.6÷2-3 ያለውን ምክር የሚዘነጉት አይደሉምና፡፡

ሠለስቱ ምእት በጉባኤ ኒቅያ የደነገጉት የሃይማኖት መግለጫ ዶግማ ይህን መሠረት ያደረገ ነበር፡፡ ጉባኤ ኤፌሶንም በቀደሙት ሁለት ጉባኤያት የተረቀቁት አናቅጽ ላይ እንዳይጨመር እንዳይቀነስ በሚል አጸናው፡፡ ከዚህ በኋላ ሊቃውንት እነዚህን ድንጋጌዎች መሠረት አድርገው እያብራሩ እያስፋፉ በመጻፍ ምእመናንን በትምህርት አንጸዋል፤ ለሰማዕትነትም አብቅተዋል፡፡ በቀደመው መሠረት ላይ የታነፀ እውነተኛ ሕንፃም ይህ ነው፡፡ ከዚህ የወጣው ግን በእሳት በሚፈተንበት ጊዜ ገለባነቱ በመቃጠል ይገለጣል፡፡ 1ኛቆሮ.3÷10-15፡፡

«ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት» በሚል ርእስ የተዘጋጀው ይህ መጽሐፍም በመጀመሪያ የሚተነትነው በሦስቱ ጉባኤያት ላይ የተደነገጉትን አሥራ ሁለቱን አናቅጸ ሃይማኖት ነው፡፡ ከዚህም በኋላ ሕግጋትን /ሕገ ልቡናን፣ ሕገ ኦሪትንና ሕገ ወንጌልን/ እያዋሐደና እያመሰጠረ «እኔ ክርስቶስን እንድመስል እናንተም እኔን ምሰሉ፡፡» 1ኛቆሮ.11÷1 በማለት ቅዱስ ጳውሎስ የሰበከለትን የሁላችንም መሪ ፊታውራሪ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንመስል ክርስቲያናዊ ሕይወትን በሰፊው ይተነትናል፤ ይልቁንም «ከሁሉም የሚበልጥ» የተባለውን «ሕገ ተፋቅሮን» በአጽንኦት ይገልጣል፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ የእነዚህን ዓይነት መጻሕፍትን አጠቃላይ ጠቃሚታ የተናገረው በሁለት ከፍሎ ነበር፡፡ የመጀመሪያውን «... ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብና ትምህርት የሚሰጡ» በማለት በሃይማኖት የምን ጸናባቸው መሆናቸውን ከገለጠ በኋላ ሁለተኛውን ደግሞ «የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ ... ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር» በማለት ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን ያላቸውን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ዘርዝሮ አስቀምጦልናል፡፡ 2ኛጢሞ.3÷14-17፡፡

ይህ መጽሐፍም ከጥንቶቹ ሊቃውንት፣ በመካከለኛው ዘመንና በአሁኑ ዘመን ያሉትንም ሊቃውንት ትርጓሜና ትምህርት እንደ አበባ ቀስሞ እንደ ማር አጣፍጦ የሚያቀርብ የሃይማኖት ድንጋጌን /ዶግማን/ በስፋትና በጥልቀት የሚተነትን ምግባረ ወንጌልንም የሚያስተምር በመሆኑ ለሊቃውንቱ ለበለጠ የምርምርና የጽሑፍ ሥራ በምንጭነት፣ ለመምህራን በማጣቀሻነት፣ ለሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች ደግሞ በቋሚ መረጃነት የሚያገለግል ጥልቅ መጽሐፍ ነው፡፡ ይልቁንም መጽሐፉ የመጀመሪያው ረቂቅ ከተሠራ በኋላ እየታሸና እየተመሟጠረ በዝግጅት ብቻ ከአሥር ዓመታት በላይ የፈጀ፣ በእነዚህ ዓመታት ብዙ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እየተመለከቱ አስተያየት የሰጡበት፣ ወጣት ሰባክያንም ጥያቄዎቻቸውንና አሳባቸውን በመሰንዘር በየጊዜው በምሥጢር እንዲጕለምስና በይዘት እንዲያድግ ያደረጉት ስለሆነ ጠቀሜታው በዚህ አጭር መግቢያ ከሚገለጸው በላይ ነው፡፡ ከመጽሐፉ መደበኛ ይዘት (text) በተጨማሪ ከመቶ በላይ ጥልቅና ምሥጢራዊ የሆኑ የግርጌ ማስታዎሻዎችን (foot notes) የያዘው ይህ መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያናችን እስካሁን የምታስተምረውን ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት በስፋትና በጥልቀት በአንድ ይዘት በማቅረብ የመጀመሪያው ይመስላል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ በመምህራን፣ በካህናትና በምእመናን እጅ ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ሰው እጅ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

በመጨረሻም የመጽሐፍ ዝግጅቱ በወሰዳቸው ጥቂት በማይባሉት በእነዚህ ዓመታት የእግዚአብሔር ረዳትነትና ተአምር በግልጽ ታይቷል፡፡ ስለዚህም አስቀድመን በኀሊና ለመታሰቡ በአንደበት ለመነገሩ ስመ ባሕርዩ የእግዚአብሔር አምላካችን፣ ስመ ሥጋዌው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ከፍ ከፍ ይበል ይክበር ይመስገን እንላለን፡፡ በመቀጠልም በእርሱ ፈቃድ በረዳትነቱም በእነዚህ ዓመታት ውስጥ መጽሐፉን ያለመሰልቸት እየተመለከቱ አስተያየታቸውን ለሰጡት ሊቃውንት ሁሉ ይልቁንም ደግሞ በእነዚህ ሁለት የመጨረሻ ዓመታት በተለያዩ ጊዜያት በፍጹም ልባዊ ፈቃድና በእውነተኛው የክርስትና ፍቅር ተይዘው በማረምና አስተያየታቸውን በመስጠት እንዲሁም አድካሚውን የጽሕፈት፣ የለቀማና የቅርጽ (formatting) ሥራ የሠሩትን ማንኛውንም ድጋፍና ምክር የለገሡትን ሁሉ በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን፡፡

*የኅትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል*

*ማኅበረ ቅዱሳን*

www.eotc-mkidusan.org

# የአርእስት ማውጫ

**ርእስ** **ገጽ**

ምዕራፍ ሁለት

## ሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን

ሀ. አዲስ ሕይወት የሚያስገኙ ምስጢራት ........ 245
1. ምስጢረ ጥምቀት ........ 245
2. ምስጢረ ሜሮን ........ 249
3. ምስጢረ ቁርባን ........ 252

ለ. አገልግሎትንና አንድነትን የሚያጠናክሩ ምስጢራት ........ 257
4. ምስጢረ ክህነት ........ 258
5. ምስጢረ ተክሊል ........ 264

ሐ. የነፍስና የሥጋ ፈውስ ምስጢራት ........ 266
6. ምስጢረ ንስሐ ........ 267
7. ምስጢረ ቀንዲል ........ 272

# ምዕራፍ ሁለት

## ሰባቱ ምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን

ለሥጋ ሕይወታችን ልደት፥ እድገትና ሌሎችም ነገሮች እንዳሉት መን ፈሳዊ ሕይወታችንም እንደዚሁ ይኸንኑ የሚመስሉ ሁኔታዎች አሉት፡፡ በዚህ መሠረት አንድ ሰው መንፈሳዊ ልደትን የሚያገኘው በእምነትና በምሥጢረ ጥምቀት እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ከዚህም ቀጥሎ ምሥጢረ ሜሮንና ምሥጢረ ቁርባን በተከታታይ ይፈጸማሉ፡፡ እነርሱም መንፈሳዊ ልደታችንንና እድገታችንን ከፍጹምና ያደርሱታል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሦስቱ አዲስ ሕይወትን የሚያሰጡ ክርስቲያናዊ ሕይወትን የሚያስገኙ ምሥጢራት ይባላሉ፡፡ እነርሱንም በአንድ ወገን መድበን በመጀመሪያ እንመለከታቸዋለን፡፡

በሁለተኛው ምድብ የአገልግሎትና የአንድነት ጸጋ የሚገኝባቸውን ምሥጢረ ክህነትንና ምሥጢረ ተክሊልን በአንድ ወገን አድርገን እናያቸዋለን፡፡

ክፋት በነገሠበት መከራና ችግር በበዛበት ደስታና ኀዘን በሚፈራረቁበት በዚህ ዓለም ውስጥ ስንኖር ለልዩ ልዩ ፈተና መጋለጥ አይ ቀርምና ነፍስ በኃጢአት፥ ሥጋም በደዌ በተያዙ ጊዜ ለሁለቱም ፈውስ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለነዚህም ችግሮች መንፈሳዊና ሥጋዊ መፍትሔ እንዲሆኑ ምሥጢረ ንስሐ ለፈውሰ ነፍስ ምሥጢረ ቀንዲል ለፈውሰ ሥጋ እንዲያገለግሉ ተዘጋጅተዋል፡፡ ስለዚህ እነርሱን በምድብ ሦስት የፈውስ ጸጋ የሚገኝባቸው ምሥጢራት በማለት እንደ ዓይነታቸው በመለየት ከሙሉ በከፊሉ እናጠናቸዋለን፡፡ እንግዲህ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በተገለጸው አመ ዳደብና ቅደም ተከተል ከብዙው በጥቂቱ እንደሚከተለው ለመግለጽ እን ሞክራለን፡፡

### ሀ) አዲስ ሕይወትን የሚያስገኙ ምሥጢራት

ከላይ እንደ ገለጽነው ሦስቱ ምሥጢራት ማለት ጥምቀት፥ ሜሮንና ቅዱስ ቁርባን በክርስቶስ ጸጋ ለተገኘው አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት (ክርስቲያናዊ ሕይወት) መሠረት ስለሆኑ ከሌሎቹ ምሥጢራት ሁሉ በማስቀደም መጀመሪያ መማር ይገባናል፡፡ ከሦስቱ ደግሞ የሚቀድመው ጥምቀት ነው፡፡ ምክንያቱም እምነት ከሁሉ ነገር እንደሚቀድም ጥምቀት ደግሞ እንደዚሁ በክርስቶስ ያለንን አንድነትና እምነት የሚመሰክርልን የእምነት ምሥጢር ስለሆ ነ በመጀመሪያ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ ጥምቀት የምሥጢራት ሁሉ መጀመሪያ፥ ወደመንፈሳዊ ነገር ሁሉ መግቢያ በር ነው፡፡

#### 1. ምሥጢረ ጥምቀት

##### የጥምቀት ትርጉምና ምሥረታ

ጥምቀት ማለት ከአዳም የወረስነውን ኃጢአትና እኛም የፈጸምነውን በደል ሁሉ ደምስሶ በመንፈስ ቅዱስ እንደገና እንድንወለድ የሚያደርገን የመጀመሪያው የጸጋና የእምነት ምሥጢር ነው፡፡ ይህም የሚፈጸመው ካህኑ በጸሎተ ክርስትና መሠረት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በውኃ በአ ጠመቀ ጊዜ ነው፡፡

www.eotc-mkidusan.org

ከላይ እንደ ገለጽነው ከምሥጢራት ሁሉ ጥምቀት ይቀድማል፡፡ ምክን ያቱም ማናቸውም መንፈሳዊ ሥራዎች ሁሉ በመንፈሳዊ ልደት መጀመር ስላለባቸው ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጅነት፥ የቤተ ክርስቲያን አባልነትና የመን ፈስ ቅዱስ ሱታፌ የሚገኘው በምሥጢረ ጥምቀት ነው፡፡ ሥጋዊ ልደት አንድ ጊዜ ብቻ እንደሆነ እንዲሁም መንፈሳዊ ልደት አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ምሥጢረ ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ ይፈጸማል እንጂ አይደገምም፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም አንዲት ጥምቀት ብቻ እንዳለች ጽፏል (ኤፌ.4፥5)፡፡

ጥምቀትን ጌታ መሥርቷል፡፡ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ እንድንጠመቅ በተግባር አስተምሮናል፡፡ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር መንግሥተ ሰማያት እንደማይገባ ተደንግጓል (ዮሐ.3፥5)፡፡ ወደ ዓለም ሁሉ ሄደው እንዲያስተምሩና በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ ክርስቶስ ሐዋርያትን አዝዟቸዋል (ማቴ.28፥18-19)፡፡

## *የጥምቀት ምሳሌ ከብሉይ ኪዳን*

ለምሥጢረ ጥምቀት ምሳሌ ሆነው የሚነገሩ ከብሉይ ኪዳን የሚገኙ ታሪኮች አሉ፡፡ ከነዚህም አንዱ የኖኅ መርከብ እንደሆነ ቅዱስ ጴጥሮስ ያስተምረናል (1ጴጥ.3፥20-21)፡፡ ሊቃውንት አባቶቻችን እንደሚተረጉሙልን ኖኅና ቤተሰቡ የምእመናን ምሳሌ፥ መርከቢቱ የቤተ ክርስቲያን፥ ውኃው የጥምቀት ምሳሌ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ክርስቶስ በሠራት መርከብ ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጥምቀት የጸጋ በር ያልገባ ሁሉ ከውጭ ስለሚቀር መዳንን አያገኝም፡፡ ከሐዋርያው ጳውሎስም ከብሉይ ኪዳን የተወሰዱ ሌሎች ሁለት ምሳሌዎችን እንማራለን፡፡ አንደኛው ምሳሌ ግዝረት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከላይ እንደ ተጠቀሰው እሥራኤላውያን ከግብፅ ሲወጡ ይመራቸው በነበረው ደመና ሥር መሆናቸውና እንዲሁም በቀይ ባሕር ውስጥ ማለፋቸውን የሚመለከት ታሪክና ምሳሌ ነው፡፡ ይህም የምሥጢረ ጥምቀት ምሳሌ እንደሆ ነ ከላይ ተመልክተናል (ቆላ.2፥11-12፤ 1ቆሮ.10፥1-2)፡፡ ከዚህም ሌላ የኢ ዮብና የንዕማን በዮርዳኖስ ተጠምቀው መዳናቸው እንደ ምሳሌ ተቆጥሯል (2ኛ ነገ.5፥1-16)፡፡

ስለ ጥምቀት ታሪክና ምሳሌ ብቻ ሳይሆን ትንቢትም ተነግሯል (መዝ.113፥3፤ ሕዝ.36፥25፤ 47፥1-12 ተመልከት)፡፡

## *በሚታየው ሥርዓተ ጥምቀት የማይታየው ጸጋ ይሰጣል፡፡*

እንደ ሌሎቹ ምሥጢራት ሁሉ፥ ጥምቀትም በሚታዩት ምልክቶችና መንፈሳዊ አገልግሎቶች አማካኝነት የማይታየውን ጸጋ ያስገኛል፡፡ ይህም ማለት በጸሎተ ክርስትና ጊዜ ካህኑ ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ሥርዓቱን ሲፈጽም ተጠማቂውን ከውኃ ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ በማድረግ ሲያጠምቀው ይታያል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ጥምቀት የሚያስገኝልን የማይታዩት የእግዚአ ብሔር ጸጋ የተባሉት የኃጢአት ሥርየት (የሐዋ.ሥራ 2፥38) ፥ ሁለተኛ ልደት (ዮሐ.3፥3-5፤ ቲቶ 3፥5)፥ ድኅነት (ማር.16፥16) ቅድስናና የመሳሰሉት ናቸው (ኤፌ.5፥25-26፤ ገላ3፥24-27)፡፡ እነዚህ መለኮታዊ የጸጋ ስጦታዎች ሲሰጡ አ ይታዩም፤ እንደ ግኡዝ እንደ ግሡስና ግዙፍ ነገር በአካላዊ ስሜቶቻችንም ልናውቃቸው አንችልም፤ በእግዚአብሔር አምነንና በቃል ኪዳኑ ተመሥርተን እንቀበላቸዋለን እንጂ፡፡ ሆኖም በእነርሱ ምክንያት ዓለማዊ አስተሳሰባችን ይቀራል፤ አዲስ ልቡና እናገኛለን፤ መንፈሳዊ ሕይወታችን ይጠናከራል፡፡ በዚህና

በመሳሰሉት መንገድ በክርስቲያናዊ ሕይወታችን ውስጥ ለውጥ ይታያል፡፡ በጸጋ ውስጥ መሆናችንንም በዚህ እናውቀዋለን፡፡ ጌታ "ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ" ብሎናልና (ማቴ.7፥20)፡፡

በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጥምቀትን የሚፈጽሙት ቀሳውስት ውኃውን በፃሕል አድርገው፥ ጸሎተ ክርስትናን አድርሰው፥ ሥርዓተ ቅዳሴን ፈጽመው በመጨረሻ "አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ" ብለው በባረኩት ጊዜ ውኃው ተለውጦ በዕለተ ዓርብ ከጌታችን በጦር ከተወጋው ጐኑ የፈሰሰውን የሕይወት ውኃ ይሆናል፡፡ በዚህም ማየ ገበ ተጠምቀው ክርስቲያኖች ከፍዳ ይድናሉ፥ ከሥላሴ ረቂቅ ልደትን ያገኛሉ ማለት በመንፈስ ይወለዳሉ፡፡ ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው የተባለው ይፈጸማል (ዮሐ.3፥6)፡፡ ከዚህ ሥርዓት የምንማረው ጥምቀት ከጌታ ሞት ጋር የተያያዘና የማይለያይ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም በመስቀል ላይ በፈሰሰው በጌታ ደም ኃጢአታችን እንደተሠረየ ሁሉ እን ደዚሁም ከጐኑ በፈሰሰው ውኃ ተጠምቀን ከኃጢአታችን እንነጻለን፡፡ ሁለቱም አንድ ስለሆኑ ጥምቀትና ቁርባን በተከታታይ ይፈጸማሉ፡፡

በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት በመጀመሪያ ጥምቀት ቀጥሎ ሜሮን ከዚያ ቁርባን መቀበል ግዴታ ነው፡፡ እነዚህንም የተቀበሉት ምእመናን ሁሉ ክርስቲያንነታቸውን የሚያስመሰክሩት በእነዚህ በሦስቱ ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ እንደ ጻፈው "የሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃው ደሙም ሦስት ናቸው፤ሦስቱም አንድ ናቸው" (1ኛዮሐ.5፥8) በማለቱ ሦስቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የክርስቲያንነት ማረጋገጫ ምስክሮች መሆናቸውን ያመለክታል፡፡

## *ጥምቀት ከጌታ ሞትና ትንሣኤ ጋር ያስተባብረናል*

ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር የሞቱም የትንሣኤውም ተካፋይ መሆኑን ለተጠማቂዎች በሚከናወነው የጥምቀት ሥርዓት ለመማር እንችላለን፡፡ ተጠማቂው ከውኃው ውስጥ መግባቱ ከጌታ ጋር መሞቱንና መቀበሩን ያመለክታል "የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እን ደተጠመቅን አታውቁምን? . . . ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን" (ሮሜ.6፥3-4)፡፡ ከውኃው ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ማለቱ ጌታ በመቃብር ውስጥ ሦስት ቀንና ሌሊት መቆየቱን ያስረዳል፡፡ በሦስተኛው ከውኃ መውጣቱ ጌታ በሦስተኛው ቀን ከመቃብር ለመውጣቱ ማስረጃ ነው፡፡ እንደዚሁም ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር ይነሣሉ፡፡ በመጀመሪያ የነፍስ ትንሣኤን ያገኛሉ፤ በመጨረሻ ደግሞ ነፍስና ሥጋቸው ተዋሕደው ይነሣሉ፡፡ የነፍስ ትንሣኤ የተባለው በእምነትና በጥምቀት የምናገኘው የትንሣኤ ልቡና ጸጋ ነው፡፡ በነፍስ ነገት መግባትን ያመለክታል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጥምቀትን ከጌታ ሞትና መቃብር ጋር አወዳድ ሮ ክርስቲያኖች ጌታን በሞቱ ከመሰሉት በትንሣኤውም እንደሚመስሉት አስ ረድቶናል (ሮሜ.6፥5)፡፡

የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከእኛ ሕይወት ጋር እንዴት እን ደሚዛመድና እንዴትስ በተግባር ልንገልጸው እንደምንችል መማር አለብን፡፡ በመጀመሪያ በኃጢአታችን የመጣውን የሞት ፍርድ በእኛ ምትክ ስለ እኛ ሆኖ መሞቱን እናምናለን፡፡ እንግዲህ ይህንን ካመንን ከአዳኛችን ጋር የጠበቀ አንድነት አለን ማለት ነው፡፡ በክርስቶስ ሞት አንድ መሆናችን የሚገለጸው ከኃጢአት ሥራ መሞታችን፥ ከክፉ ነገር መለየታችን ለመሆኑ

www.eotc-mkidusan.org

ከቅዱስ ጳውሎስ እንማራለን፡፡ "የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ" (ገላ.5፥24) የተባለው ቃል ኃጢአትን እንደ ሞተ እንደ ተቀበረ እንድንቆጥረው ያመለክተናል፡፡ ከክርስቶስ ጋር መሞትና መቀበር ማለት ፈቃደ ሥጋንና ፈቃደ ሰይጣንን መዋጋትና መጋደል ከዓለማዊም ደስታ ራሳችንን መለየት መሆኑን የጥምቀት እውነተኛ ትርጓሜ ያስረዳናል፡፡ "እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ" (ሮሜ.6፥12)፡፡

በጥምቀት ከኔታ ሞት ጋር አንድ የመሆናችንና በትንሣኤውም የመተባበራችን ትርጉም ምን እንደሆነ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያስረዳናል፡፡ "ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤ ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደተሰቀለ እናውቃለን፤ የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቋልና፡፡ ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን" (ሮሜ.6፥5-8)፡፡

እንግዲህ የተጠመቅን ክርስቲያኖች አሮጌውን ሰው ማለት የድሮውን ክፉ ጠባያችንንና የኃጢአት ሥራችንን ከክርስቶስ ጋር ሰቅለን ማለት እንደ ሞተ ሰው ያህል ተለያይተን በክርስቶስ እንደ አዲስ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ተወልደን አዲስ የጸጋ ሕይወትን መኖር እንዳለብን እንማራለን፡፡ ስለዚህም እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ከክርስቶስ ጋር የጠበቀ የመንፈስ ቅዱስ ግንኙነት ይኑረን፡፡ እያንዳንዱ ክርስቲያንም በመንፈስ ከእርሱ ጋር እንዲህ ይበል፡፡ "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው" (ገላ.2፥20)፡፡

## *ሕፃናትን በወቅቱ ማጥመቅና በትምህርት ስለ ማሳደግ*

እኔ የተጠመቅሁት በሕፃንነቴ ስለሆነ ይኸንን ሁሉ አላውቅም ማለት በቂ አይደለም፡፡ ይልቅስ ተምሮ የተማሩትን በሥራ ላይ ማዋል ትልቅ ቁም ነገር ነው፡፡ በጥንተ አብሶ የተላለፈው ፍዳና መርገም ሕፃናትን ሁሉ ስለሚመለከት በወቅቱ መጠመቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በወላጆች ወይም በካህናት ቸልተኝነት ሕፃኑ ሳይጠመቅ ቢሞት በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት ይቀጣሉ (ፍት.ነገ.አንቀጽ 3)፡፡ በጥንት ጊዜ መላው ቤተሰብ ማለት አዋቂዎችም ሕፃናትም እንደሚጠመቁ በታሪክም በቅዱሳት መጻሕፍትም ይገኛል (የሐዋ.ሥራ 10፥48፤ 16፥15፤ 1ኛቆሮ.1፥16)፡፡

በኦሪት የቃል ኪዳን ምልክት የሆነው ግዝረት ሕፃናት በተወለዱ በስምንተኛው ቀን ይፈጸም ነበር (ዘፍ.17፥7-14)፡፡ ስለ ቃል ኪዳን ምንም በማያውቁ ሕፃናት እንደዚህ የግዝረት ሥርዓት የሚፈጸም ከሆነ የጥምቀትንም ሥርዓት ለሕፃናት መፈጸም ተገቢ ነው፡፡ ግዝረት ለጥምቀት ምሳሌ ነውና (ቆላ.2፥11-12)፡፡

ሕፃናት ሳያውቁ በሥጋ እንደ ተወለዱ እንደዚሁም ሳያውቁ መንፈሳዊ ልደትን በጥምቀት ያገኛሉ፡፡ አለማወቅ የጸጋን ምሥጢር አይገድበውም፡፡ በእናታቸው ማኅፀን እንኳ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ እንዳሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ (ኤር.1፥5፤ ሉቃ.1፥44)፡፡ ከዚህም ሌላ ሕፃናት ወደ ክርስቶስ እንዳይመጡ መከልከል አይገባም (ማቴ.19፥14)፡፡ ይልቅስ ሕፃኑን

www.eotc-mkidusan.org

በክርስቶስ ጸጋና እውቀት ማሳደግ ታላቅ ቁም ነገር ነው፡፡

ስለዚህ ወላጆች በተለይም የክርስትና አባቶችና እናቶች ክርስትና ያነሡአቸውን ሕፃናት በሃይማኖት ትምህርት እንዲያሳድጓቸው፥ በመልካም ምግባር እንዲያንጿቸው ያስፈልጋል፡፡ ካህናትም ምእመናን ሁሉ ምሥጢረ ጥምቀትን እንዲያውቁ፥ ቃለ እግዚአብሔርን እንዲማሩ ማድረግ ከቅዱሳን ሐዋርያት የተረከቡት ሥልጣንና ሥራ መሆኑን ተገንዝበው ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንዲተጉና ይህም ሐዋርያዊ ተልእኳቸው ታላቅ ኃላፊነትና አደራ ያለበት መሆኑን መዘንጋት አይገባቸውም፡፡

የክርስትና አባትና እናት የሚሆኑትን ምእመናን በቅድሚያ አውቆ አስ ፈላጊውን ምክርና ትምህርት በመስጠት ጸሎተ ሃይማኖትን በቃል እንዲያጠኑ፥ ትርጉሙንም እንዲያውቁ፥ የቤተ ክርስቲያንንም ምሥጢራት በትክክል እን ዲረዱ ማድረግ የካህናት ሁሉ ኃላፊነት ነው፡፡ የክርስትና ልጆችንም በሃይማኖትና በሞራል ትምህርት የማሳደግ ኃላፊነት የተጣለው በክርስትና አባ ትና እናት ላይ መሆኑ ሁሉም እንዲያውቁት ያስፈልጋል፡፡ የሥጋ ወላጆችም ልጆቻቸው የሃይማኖት ፍቅር እንዲያድርባቸውና የቤተ ክርስቲያንንም ሥርዓት እየተለማመዱ እንዲያድጉ ማድረግ የዘወትር ጥረታቸው መሆን ይገባዋል፡፡ እያንዳንዱ ቤተሰብ እንደ ቤተ ክርስቲያን ስለሚቆጠር የጠዋትና የማታ ጸሎት በግልም ሆነ በአንድነት ማድረግ፥ ከዚህም ጋር የማእድ ጸሎትን ማድረስ ለቤተ ሰቡ አባላት ሁሉ ጸጋና በረከትን ያስገኛል፡፡ ሕፃናትንም አብረው እንዲጸልዩ ማበረታታትና ከክፉ ነገርም እንዲቆጠቡ በፍቅርና በጥበብ መክሮና አስተም ሮ ማሳደግ የወደፊት ኑሯቸው እንዲቃና ከማድረጉም በላይ ወላጆቻቸውን በነፍ ስም በሥጋም ይጠቅማቸዋል፡፡

## 2. <u>ምሥጢረ ሜሮን</u>

### *<u>ትርጉሙና አመሠራረቱ</u>*

ሜሮን ማለት ከጥምቀት ጋር ከጥምቀት ቀጥሎ የሚፈጸም መንፈስ ቅዱስን የሚያሰጠን፥ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቃችንን፥ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ መወለዳችንን የሚያረጋግጥልን ታላቅ ምሥጢር ነው፡፡ ጌታችን ከዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ሲወጣ መንፈስ ቅድስ እንደ ወረደና የባሕርይ ልጅ ነቱ እንደ ታወቀ እንዲሁም ተጠማቂዎች በምሥጢረ ሜሮን የጸጋ ልጅነትን ማግኘታቸው ይረጋገጣል፡፡ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ መወለዳቸው ይታወቃል፡፡ በዚህም የክርስቶስን አርአያ ይከተላሉ፡፡ እንግዲህ በምሥጢረ ጥምቀትና በምሥጢረ ሜሮን አማካኝነት አማኞች ከክርስቶስ ጋር አንድ ይሆናሉ፥አዲስ የመንፈስ ቅዱስ ሕይወትንም ይጀምራሉ፡፡

ምሥጢረ ሜሮንን ማን መሠረተ? ከክርስቶስ በስተቀር ሌላ መሥራችም ሌላ መሠረትም የለም፡፡ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስን የሚሰጥና የሚያሰጥ እርሱ ብቻ ነውና፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ እንደ መሰከረለት በመንፈስ ቅዱስና በእሳት የሚያጠምቅ ክርስቶስ እንደሆነ እንመለከታለን (ሉቃ.3፥16)፡፡ ለሐዋርያትም ጰራቅሊጦስን ማለት የሚያጽና የሚያጽናና ወደ እውነት ሁሉ የሚመራቸው መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ተስፋ ሰጣቸው (ዮሐ.14፥26፤ 16፥7-15)፡፡ ከዕርገቱም በኋላ በአሥረኛው ቀን በበዓለ ኀምሳ በተስፋው መሠረት መንፈስ ቅዱስን ላከላቸው፡፡ በመንፈስ ቅዱስም አጠመቃቸው (የሐዋ. ሥራ1፥5፤ 2፥1-4)፡፡ ዛሬም በምሥጢረ ሜሮን ለተጠማቂዎች የሚሰጠው ለሐዋርያት የተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ነው፡፡

www.eotc-mkidusan.org

መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ሐዋርያት መጽናናትን ብርታትን አገኙ፡፡ አዲስ ሕይወትንም ጀመሩ፡፡ ኃይልንና ተአምራትን በሰጣቸው በመንፈስ ቅዱስ በበዓለ ኀምሳ ለተሰበሰቡት ሁሉ በልዩ ልዩ ቋንቋ ወንጌልን ሰበኩላቸው፡፡ ሕዝቡም "ይህንንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት፦ ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ? አሏቸው፡፡ ጴጥሮስም፦ ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ትቀበላላችሁ" (የሐዋ.ሥራ2፥37-38)፡፡ እንግዲህ ከዚህ ጥቅስ እንደምንማረው ሐዋርያት እያጠመቁ መንፈስ ቅዱስን የሚያስጡ ሆነዋል፡፡ ዛሬም ቤተ ክርስቲያናችን ጥምቀትንና ምሥጢረ ሜሮንን የምትፈጽመው የሐዋርያትን ሥራና ትውፊት በመከተል ነው፡፡

ከሐዋርያት ሥራ እንደምንማረው አዲስ አማንያን እንደ ተጠመቁ ሐዋርያት እጃቸውን በተጠማቂዎቹ ራስ ላይ በማኖር ሲጸልዩላቸው መንፈስ ቅዱስ ያድርባቸዋል፡፡ ጴጥሮስና ዮሐንስም ለሰማርያ ምእመናን ያደረጉት ይህንኑ ነው (የሐዋ.ሥራ 8፥16)፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስም ኤፌሶን ለሚገኙ በቁጥር አሥራ ሁለት ያህል ለሚሆኑ ሰዎች በአንብሮተ እድ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ አድርጓል፡፡ ጳውሎስም እንዲህ ብሎ ጠይቋቸው ነበር፦

> "ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን? አላቸው፡፡ እነርሱም፦ አልተቀበልንም፤ መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ስንኳ አልሰማንም አሉት፡፡ እንኪያ በምን ተጠመቃችሁ? አላቸው፡፡ እነርሱም፦ በዮሐንስ ጥምቀት አሉት፡፡ ጳውሎስም፦ ዮሐንስስ ከእርሱ በኋላ በሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ ዘንድ ለሕዝብ እየተናገረ በንስሐ ጥምቀት አጠመቀ አላቸው፡፡ ይህንንም በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ፤ ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ፥ ትንቢትም ተናገሩ" (የሐዋ.ሥራ19፥2-6)፡፡

## <u>*ቅብዐ ሜሮን በብሉይና በሐዲስ ኪዳን*</u>

ከላይ እንደ ተመለከትነው መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት አማካኝነት በአንብሮተ እድ ይሰጥ ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በቀሳውስት አማካይነት በቅብዐ ሜሮን ይፈጸማል፡፡ "ሜሮን" የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ "ቅብዐት" ማለት ነው፡፡ በተቀደሰው ቅብዐት የመቀባት ሥርዓት በኦሪት ሕግ የተደነገገ ነው፡፡ ካህናቱና የመቅደሱ ንዋያተ ቅድሳት በተቀደሰው ቅባት እንደሚቀቡና በዚህም ምክንያት እነርሱም የተከበሩና የተለዩ የተቀደሱም እንደሚሆኑ ተጽፏል (ዘፀ.30፥22-38)፡፡ ይህም ለሐዲስ ኪዳኑ ሥርዓት ለምሥጢረ ሜሮንና ለቅብዐ ቅዱስ ሁሉ ምሳሌ ሆኗል፡፡ የብሉይ ኪዳኑ ቅብዓት ሰዎችን ለእግዚአብሔር የተለዩና ለአገልግሎቱም የተመረጡና የተቀደሱ ብቻ ለማድረግ ሳይሆን፣ ሁሉን የሚቀድሰው መንፈስ ቅዱስ በሐዲስ ኪዳን ለመሰጠቱም ጭምር ምሳሌነት አለው፡፡ ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ቅዱስ ቅባት ሲል አማኞችን የሚቀድሰውና ለአማኞችም የተሰጠውን መንፈስ ቅዱስን ያሳያል፡፡

> "እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፥ ሁሉንም ታውቃላችሁ፡፡ . . . እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፥ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፥ እውነተኛም እንደሆነ ውሸትም እንዳልሆነ፥ እናንተንም እንዳስተማራችሁ፥ በእርሱ ኑሩ" (1ኛዮሐ.2፥20-27)፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለዚሁ ጽፏል፦ "በክርስቶስ ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው፥ ደግሞም ያተመን የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው" (2ኛቆሮ.1፥21-22)፡፡

www.eotc-mkidusan.org

## በምሥጢረ ሜሮን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን እንቀበላለን

ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚደረገውና በሚታየው የቅብዐ ሜሮን ሥርዓት አማካይነት የማይታየው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ይሰጣል፡፡ ቅዱሱንም ቅባት ለተቀበሉት ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ እንደ ገለጸው መንፈስ ቅዱስ ስለ ሁሉ ነገር ያስተምራቸዋል (1ኛዮሐ.2፥27)፡፡ መንፈስ ጽድቅ አድሮባቸዋልና ወደ ትክክለኛው ነገር ሁሉ ይመራቸዋል (ዮሐ.16፥13)፡፡ የክርስቶስን መስቀል ተሸክመው እንዲከተሉት ያበቃቸዋል፡፡ እስከ መጨረሻው በትዕግሥት እንዲጸኑ ያደርጋቸዋል፡፡ እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ በጥምቀት ጊዜ በመንፈስ እንድንወለድ ከማድረግ ጀምሮ በክርስቶስ ጸጋ እንድናድግና የሃይማኖት ፍሬ እንድናፈራ የሚያበቃን እርሱ ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስን የተቀበለ ምእመን የመንፈስ ቅዱስ ሀብታት ያድሩበታል፡፡ “ የእግዚአብሔር መንፈስ፥ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፥ የምክርና የኃይል መንፈስ፥ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል” (ኢሳ.11፥2)፡፡ በእነዚህ ሀብታት የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቅበት፥ የሃይማኖትን ምሥጢራት የምናስተውልበት፥ መልካሙንና የሚበልጠውን መንገድ ለመምረጥ ምክርን የምናገኝበት፥ ክፋውን ለማስወገድ ኃይል የሚሆኑንና መልካሙንም ሥራ እንድናከናውን የሚያበቁን መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ ስለዚህ ክርስቲያኖች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እየተመሩ በመልካም ሥራቸው የሰማይ አባታቸውን በሰዎች ዘንድ እንዲመሰገን በማድረጋቸው ክርስቲያናዊ ሕይወታቸው በዘልማድ ሳይሆን በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡

መንፈስ ቅዱስን መቀበል ቀላል ነገር አይደለም፡፡ ምክንያቱም እኛን ለማዳን ክርስቶስ በተቀበለው ሕማምና ሞት የተገኘ ታላቅ ጸጋ ነው እንጂ እንዲያው በከንቱ ወይም በአጋጣሚ የመጣ አይደለምና፡፡ እንዲህማ ካሰብን የእግዚአብሔርን ፍቅርና ውለታ ረሳን ማለት ነው፡፡ የእውነት መንፈስ የለብንም ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር እኮ እኛ ሳናውቀውና ሳንወደው እርሱ በመጀመሪያ እንዲሁ ወደደን፥ ልጁን ወደ ዓለም ልኮ በእርሱ ሕማምና ሞት እንድንድን አበቃን፡፡ ከዚያም፥ በሰጠን ሃይማኖት ሳንፈራ በትዕግሥት እንድንኖር የሚያጸናን ፥ በመከራችንና በችግራችን የሚያጽናናን፥ በጨለማው ዓለም በምንኖርበት ጊዜ ከተሰፋው ሀገር እስክንገባ ድረስ በእውነተኛው መንገድ የሚመራን መንፈስ ቅዱስን ላከልን፡፡ ይህን ሁሉ ያደረገ እግዚአብሔር እኛ ከእርሱ ጋር ሆነን ያዘጋጀልንን የዘለዓለሙን ደስታና ተድላ ተካፋይ እንድንሆንለት ብቻ አስቦ የፈጸመው ነው፡፡ ስለዚህ ይኸን ሁሉ በመገንዘብ እንደዚህ የወደደንን እግዚአብሔር እኛም በሙሉ ልባችን በደስታ መንፈስ መውደድና ማመስገን ይኖርብናል፡፡

እንግዲህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ መከረን “በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ” (ገላ.5፥25)፡፡ የሥጋን ምኞት የዚህን ዓለም አምሮት ወደ ጐን ትተን ከእግዚአብሔር ጋር ሆነን ልባችንን ክርስቶስ ወደ አለበት ሥፍራ ከፍ ከፍ አድርገን፥ የተስፋይቱን ሀገር እየተመኘን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ወደፊት እንገሥግሥ፡፡ እንግዲህ አሳስፋሳጊ የሆኑትን ባሕላዊና ልማዳዊ አኗኗራችንን ትተን፥ በፈቃደ ሥጋ ሳይሆን በፈቃደ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ የማዳን ሥራ ያገኘነውን ጽድቅና ደኅንነት ጠብቀን መኖር ይገባናል፡፡ በዚህም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ወደተባሉት እንደርሳለን፡፡ እነርሱም “ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት”ናቸው (ገላ.5፥22)፡፡

በግ ደም መረጨትና ሥጋውም ተጠብሶ መበላቱ የእግዚአብሔር በግ ለተባለው ለክርስቶስ አዳኝነትና ለምሥጢረ ቁርባን ምሳሌ ሆኗል (ዘፀ.12÷1-51፤ 1ኛ ቆሮ.5÷7)፡፡ ሦስተኛው እሥራኤላውያን በምድረ በዳ ይመገቡት የነበረው ከሰማይ የወረደው መና፥ ዛሬ ምእመናን ለነፍሳቸው ምግብ የሚቀበሉት የሥጋውና የደሙ ምሳሌ ነው (ዘፀ.16÷16-23፤ ዮሐ.6÷49-51)፡፡ አራተኛው ጥበብ ያዘጋጀችው ማዕድ፥ ያረደችው ፍሪዳ፥ የጠመቀችው የወይን ጠጅ፥ የላከቻቸው አገልጋዮቿ፥ የተጠሩት ሰዎች ሁሉ ምሳሌነት እንዳላቸው ይነገራል፡፡ ጥበብ የክርስቶስ፥ ማዕድ የሥጋው የደሙ፥ አገልጋዮች የካህናት፥ ተጋባዦች የምእመናን ምሳሌ ናቸው ተብሎ ይተረጐማል (ምሳ.9÷1-5)፡፡ ይህን የመሳሰሉ ሌሎች ምሳሌዎችም አሉ (ዘሌዋ.2፤ 23÷13-14፤ ሲራክ 24÷19-21)፡፡

ትንቢትም ስለ እውነተኛው ቁርባን ተናግሯል፡፡ "ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና፤ በየሥፍራውም ለስሜ እጣን ያጥናሉ፥ ንጹሕም ቁርባን ያቀርባሉ" (ሚል.1÷11)፡፡ ይህ ስለ ወንጌል መሥዋዕት የተነገረ እንጂ ስለ ኦሪት መሥዋዕት አይደለም፡፡ ምክንያቱም የኦሪት መሥዋዕት በኢየሩሳሌም ከተማ በቤተ መቅደስ ብቻ እንጂ በሌላ ቦታ እንዳይፈጸም በሕግ የተከለከለ ነው፡፡ እንግዲህ ነቢዩ ሚልክያስ "ንጹሕ ቁርባን" ያለው እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ለአሕዛብ ወንጌል በተሰበከበት ሥፍራ ቤተ ክርስቲያን በተቋቋመበት ቦታ ሁሉ የሥጋውና የደሙ ንጹሕ መሥዋዕት መቅረቡን የሚያመለክት ነው፡፡

ሌላው ደግሞ የኢሳይያስ ትንቢት ነው፡፡ "እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ፥ ወደ ውኃ ኑ፥ ገንዘብም የሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም፤ ኑ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም የወይን ጠጅና ወተት ግዙ . . . በረከትንም ብሉ . . . " (ኢሳ. 55÷1-2)፡፡ ይህ የነቢዩ ቃል በመብልና በመጠጥ ስለሚመጣው ስለ ምሥጢረ ቁርባን በትንቢትና በምሳሌ እንደ ተነገረ ይታመናል፡፡

## *የምሥጢረ ቁርባን አመሠራረት*

ምሥጢረ ቁርባንን ጌታችን ከሕማማቱና ከሞቱ በፊት በዋዜማው ኀሙስ ማታ መሥርቶታል፡፡ ይህም ሰዓት በአይሁድ የቀን አቆጣጠር ወደ ዓርብ ይታሰባል፡፡ በዚያም ወቅት የኦሪት የፋሲካ በግ የሚሠዋበት ጊዜ በመሆኑ ጌታችን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የኦሪትን መሥዋዕት አሳልፎ መሥዋዕተ ወንጌልን መሥርቷል፡፡ በዚያች ምሽት የኦሪቱ በግ መሥዋዕትነት አበቃ፤ ከእንግዲህ ወዲህ እውነተኛው የእግዚአብሔር በግ ይሠዋል፡፡ እርሱም የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው፡፡ ስለዚህ በማዕዱ ዙሪያ ለተሰበሰቡት ሐዋርያቱ በብሉይ ኪዳን ምሳሌ የተመሰለለትን፥ ትንቢት የተነገረለትን አዲሱን ቃል ኪዳን ጌታ በራሱ ሥጋና ደም መሠረተ፡፡ የእውነተኛው መሥዋዕት ምሳሌ የሆነው የኦሪቱን ማዕድ እየበሉ ሳለ፥ "ኢየሱስ እንጀራን (ኅብስትን) አንሥቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፦ እንካችሁ፥ ብሉ፤ ይህ ሥጋዬ ነው አለ፡፡ ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፦ ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" በማለት ምሥጢረ ቁርባንን መሠረተ (ማቴ.26÷26-28)፡፡ ኪዳን ማለት ከእግዚአብሔር ጋር የምንገባውን ቃል ኪዳን የሚያመለክት ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝነት ከቤተ እሥራኤል ጋር ቃል ኪዳን የገባው በእንስሳት ደም ነበር (ዘፀ.24÷1-11)፡፡ ያን ጊዜ ቤተ እሥራኤል ቃል የገቡት ሕገ ኦሪትን ሊፈጽሙ አሠርቱ ትእዛዛትን ሊጠብቁ ሥርዓቱን ሊያከብሩ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ በበኩሉ አምላካቸውና

www.eotc-mkidusan.org

ጠባቂ.ያቸው ሊሆን፥ ምድረ ርስትንም ሊያወርሳቸው ተስፋ ሰጣቸው፥ ቃል ገባላቸው፡፡ በወንጌል ግን እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገባው በልጁ ደም ነው፡፡

እግዚአብሔርም የፈጸመልን አዲሱ ኪዳን ከብሉይ ኪዳን እጅግ የላቀ ነው፡፡ ምክንያቱም በክርስቶስ የሐዲስ ኪዳን ደም ኃጢአታችን ተወግዶልናል፤ ከእግዚአብሔር ታርቀናል፤ የእግዚአብሔርን ልጅነት አግኝተናል፤ እግዚአብሔርም አባት ሆኖን የመንግሥቱ ወራሾች እንድንሆን አብቅቶናል፡፡ ስለዚህ ይህን ወሰን የሌለው እስከ ሞት ድረስ የወደደንን የክርስቶስን ፍቅር እያሰብን፥ እግዚአብሔርን በልጁ ስም ዘወትር ለማመስገን፥ ወንድሞቻችንንም ለማፍቀርና ችግረኞችንም ለመርዳት የወንጌልንም ትእዛዝ ለመፈጸም. እኛም በበኩላችን ቃል መግባት ይኖርብናል፡፡

ቃል ኪዳን ከገባንበት ዋናው ነገር በቆረብንና ቅዳሴ ባስቀደስን ቁጥር የበደላችንንና የኃጢአታችንን ሥርየት ያገኘንበትን፥ ከእግዚአብሔር የታረቅንበትን የክርስቶስን ሕማምና ሞት ማሰብና ማስታወስ ነው፡፡ ስለዚህ ነው ጌታችን ኅብስቱን አንሥቶ ባርኮና ቆርሶ ለሐዋርያቱ ከሰጣቸው በኋላ "ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት" ብሎ ያላቸው (ሉቃ.22፥19)፡፡ መታሰቢያዬ የተባለው ስለ ሕማምና ሞቱ መሆኑንና፥ ይህንንም የሞቱን ዜና የመስቀሉን ነገር ጌታ እስኪመጣ ድረስ በምሥጢረ ቁርባን አማካኝነት እንደሚነገር ከሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንማራለን (1ኛቆሮ.11፥23-26)፡፡ ዛሬም በጸሎተ ቅዳሴ "ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ" የተባለውን እያዜምን እናስታውሰዋለን፡፡ በምንቆርብበት ጊዜ የምናየው የተፈጥሮ ኅብስትና ወይን ብቻ መስሎን እንዳንሳሳት፥ የማይታየው መለኮት የተዋሐደው የጌታ ሥጋና ደም መሆኑን አምነን መቀበል አለብን፥ አለበለዚያ በራሳችን ላይ ፍርድን እናመጣለን፡፡

ሳይገባው ራሱን ሳይፈትንና ሳይመረምር የሚቆርብ "የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና" በማለት ይኸው ሐዋርያ ያስጠነቅቀናል፡፡

> "ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ ኅብስት የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት፡፡ ሰው ግን ራሱን ይፈትን፥ እንዲሁም ከእንጀራው ከኅብስቱ ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና፡፡ ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ እያሌዎችም አንቀላፍተዋል፡፡ ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር፤ ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ፥ ከዓለም ጋር እንዳንኰነን በጌታ እንገሠጻለን" (1ኛቆሮ.11፥27-32)፡፡

## *በምሥጢረ ቁርባን የሚገኝ ጸጋ*

የሚታየው ኅብስትና ወይን በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ በክርስቶስ ቃል፥ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፥ በካህኑ ጸሎት ወደ ጌታ ሥጋና ደም መለወጣቸውን በሙሉ ልብ አምነውና በንስሐ ተዘጋጅተው ለሚቀበሉ ሁሉ በወንጌል የተጻፈውን የማይታየውን ጸጋ ለማግኘት ይችላሉ፡፡ የሚከተሉትን የእግዚአብሔር ጸጋ ማግኘት ለአማኞች ሁሉ ከፍተኛ ጥቅምና እድል ነው፡፡ የመጀመሪያው ጸጋ ሰውና እግዚአብሔርን ያራራቀውን ኃጢአትን ማስወገድ ነው፡፡ ስለዚህ ነው የቁርባን ምሥጢር ሲመሠረት ጌታችን ይህ ደሜ ነው ለብዙዎች የኃጢአት ሥርየት የሚፈሰው በማለት የጸጋውን ስጦታ የጀመረው (ማቴ.26፥27-28)፡፡ የኃጢአት ሥርየት ከተገኘ ከእግዚአብሔር ጋር እርቅና ሰላም ይወርዳል፡፡ እርቅ ከተገኘ ደግሞ ሌሎቹ ስጦታዎች ደግሞ ይጨመራሉ፡፡ ኃጢአታቸው የተተወላቸው ብፁዓን ናቸውና (መዝ.31፥1)፡፡

ከዚህ ቀጥሎ በምሥጢረ ቁርባን የምናገኘው ጸጋ ከክርስቶስ ጋር አንድ ሆነን በኅብረት መኖር ነው፡፡ ይህም ማለት እኛ በእርሱ፥ እርሱ በእኛ ይኖራል ማለት ነው፡፡ "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእር ሱ እኖራለሁ" በማለት ጌታ አረጋግጦልናል (ዮሐ.6፥56)፡፡ ነገር ግን ከቁርባን እርቀን ሥጋውና ደሙን ሳንቀበል ብንቀር በራሳችን ሕይወት አይኖረንም፡፡ ምክንያቱም አንዲት የወይን ሐረግ ከወይኑ ግንድ ተለይታ ለመኖር አት ችልምና፡፡

"ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ እውነት እውነት እላችኋለሁ የወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም" (ዮሐ.6፥53)፡፡ እንግዲህ የመጨረሻውን ጸጋ የዘላለም ሕይወትን የምናገኘው ለትንሣኤውም የምንበቃው በሥጋና በደሙ ነው፡፡ "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አሥ ነሣዋለሁ" (ዮሐ.6፥54)፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ጸጋዎች ሌላ ምሥጢረ ቁርባንን በንስሐና በጸሎት ሆኖ በሚገባ ተዘጋጅቶ የሚቀበል ሁሉ ነፍሱን ከመራብና ከመጠማት ያድናታል፡፡ ምክንያቱም ሥጋውና ደሙ እውነተኛ መንፈሳዊ ምግብ ስለሆ ነ ነው፡፡ "ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፡- የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠ ማም" (ዮሐ.6፥35)፡፡

ምሥጢረ ቁርባን የሚያስገኘው ጸጋ ሰውን ከእግዚአብሔር ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ሰውንና ሰውንም ያቀራርባል፡፡ ስለዚህ የክርስቶስን ሥጋና ደም የተቀበሉ ሁሉ እርስ በርሳቸው በፍቅር የተሳሠረ ኅብረትና አንድነት አላቸው፡፡ ምክንያቱም በቁርባኑ ሁላችንም የክርስቶስ አካልና አባል ሆነናል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ሁላችንም ከአንዱ ኅብስትና ጽዋ ተሳትፎ ስላለን ነው፡፡ "የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደ ለምን? የምንቆርሰው እንጀራ ኅብስት ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይ ደለምን? አንድ እንጀራ ኅብስት ስለሆነ፥ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ ኅብስት እንካፈላለንና፡፡ በሥጋ የሆነውን እሥራኤል ተመልከቱ፤ መሥዋዕቱን የሚበሉ የመሠዊያው ማኅበርተኞች አይ ደሉምን?" (1ኛቆሮ.10፥16-18፤ ዘሌዋ.7፥6 እና 15)፡፡ እንግዲህ ይህ ትቅስ የሚያስተምረን በሥጋውና በደሙ ሁላችን አንድ የእግዚአብሔር ቤተሰብ መሆናችንን ነው፡፡ በአፀደ ነፍስም በአፀደ ሥጋም ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ እን ደ አንዲት የተቀደሰች ማኅበር ይቆጠራሉ፡፡ ሁሉም የአንድ የክርስቶስ አካል ሆነዋልና፡፡

## ቅዱስ ቁርባን እውነተኛ መሥዋዕት ስለ መሆኑ

ቅዱስ ቁርባን ለኃጢአታችን ማስተሥረያ እንዲሆን ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መሥዋዕት ነው፡፡ የዚህንም ምሳሌ ከኦሪቱ የመሥዋዕት ሥርዓት እን ማራለን፡፡ የኦሪቱ ሊቀ ካህናት ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ የኃጢአት ማስተሥረያ የሚሆኑትን እንስሳት በመሠዋት ደሙን ከቅድስተ ቅዱሳት ገብቶ በመርጨት ከእግዚአብሔር የኃጢአትን ሥርየት ያስገኝል (ዘሌዋ.16)፡፡ ይህም በዓመት "የኃጢአት ሥርየት ቀን" ተብሎ ሕዝቡ ሁሉ በኀዘንና በንስሐ ሆነው ሃያ አ ራት ሰዓት በመጾም ያከብሩታል (ዘሌዋ.23፥26-32)፡፡ የዚህንም ትርጉም ከሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንማራለን፡፡ በዕለተ ዓርብ በመልዕልተ መስቀል እውነተኛ ሊቀ ካህናት ስለ ራሱ ሳይሆን ስለ ዓለም ኃጢአት ራሱን አንድ ጊዜ

ብቻ ሠውቶ ደሙን ይዞ በሰው እጅ ባልተሠራችው ወደ ሰማያዊት ቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ ከእግዚአብሔር የኃጢአታችንን ሥርየት አስገኝቶልናል (ዕብ.9፥11-14)፡፡ ጌታችን በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ስለ እኛ ኃጢአት ሲል ለዓለም ሁሉ ቤዛ በመሆን ሕይወቱን ማለት ሰውነቱን ለሕማምና ለሞት አሳልፎ በመስጠት ለአንዴና ለዘላለም ያቀረበውን መሥዋዕት ሁልጊዜ ለማግኘት እንድን ችል በጸሎተ ኀሙስ ማታ ጌታ ምሥጢረ ቁርባንን መሥርቶልናል፡፡ ስለዚህም በየጊዜው ስለምንፈጽመው በደል የኃጢአት ሥርየት እንድናገኝ በንስሐ ተዘጋጅተን በየጊዜው የሚቀርበውን የቅዱስ ቁርባን መሥዋዕት መቀበል ይኖርብናል፡፡

እንግዲህ ቅዱስ ቁርባን ለመታሰቢያ ብቻ የሚፈጸም፥ ያለፈውን ድርጊት ለማስታወስ ብቻ የሚደረግ እንዳይመስላችሁ፡፡ እንዳለፈና እንደሚረሳ ነገር ሳይሆን፥ የዕለተ ዓርቡ መሥዋዕት ለዘላለም ሕያው ሆኖ በምሥጢረ ቁርባን አማካይነት የጌታ ሥጋና ደም እውነተኛ ምግብና እውነተኛ መጠጥ ሆኖ ለአማንያን ሁሉ ይቀርብላቸዋል፡፡ ወደ ጌታ ሥጋና ደም የተለወጠውን ኅብስትና ወይን ነው ጌታ በጸሎተ ኀሙስ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉ ያለው፡፡ ዛሬም በጌታ ቃል በመንፈስ ቅዱስ ግብር ወደ ጌታ ሥጋና ደም የተለወጠው ኅብስትና ወይን በዕለተ ዓርብ የተፈጸመውን መሥዋዕት ሆኖ ለእግዚአብሔር ይቀርባል፡፡ ሌላ ዓይነት መሥዋዕት አይደለም የቀረበው ያው በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ የተቆረሰው ሥጋውና የፈሰሰው ደሙ ነው እንጂ፡፡ እንደዚህማ ባይሆን ኖሮ "ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው" ተብሎ የተነገረለትን ሥጋና ደም ከየት እናገኘው ነበር? (ዮሐ.6፥54)፡፡

የጌታ ሥጋና ደም እውነተኛ መብልና መጠጥ መሆኑን ከሰሙት ደቀ መዛሙርት መካከል በቁሙ የዕሩቅ ብእሲን ሥጋ እንደ መብላት አድርገው በመቁጠር ስላንጐራጐሩ የዕሩቅ ብእሲ ሥጋ ምንም እንደማይጠቅም (ዮሐ.6፥60-63) ጌታ ካስረዳቸው በኋላ የዚህን ምሥጢር እውነተኛ ትርጉም በጸሎተ ኀሙስ የቅዱስ ቁርባንን ሥርዓት በመሠረተ ጊዜ ለሐዋርያት ገልጾላቸዋል፡፡ ይህም ማለት ኅብስቱና ወይኑ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም እንደሚለወጥ አምነው እንዲቀበሉት አብቅቷቸዋል ማለት ነው፡፡ እንግዲህ ይህንን ነው ጌታ "ሥጋዬ እውነተኛ መብል፥ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው" ብሎ ከጸሎተ ኀሙስ በፊት በቅድሚያ ለደቀ መዛሙርቱ በቅፍርናሆም ከተማ በምኩራብ ያስተማራቸው (ዮሐ.6፥55-59)፡፡

እሥራኤል ከምድረ ግብፅ ነፃ የወጡበትን የፋሲካ በዓል መታሰቢያ የሚያከብሩት እንዲያው የዕለቱ ዕለት ቁጭ ብለው በመዋል ብቻ የሚያስቡት አልነበረም፡፡ በመጀመሪያ ነፃ በወጡበት ዕለት ዋዜማ ያረዱትን የነፃነታቸው መሠረት የሆነውን የፋሲካን በግ በማሰብ ሁሉም ሰው በየዓመቱ በየቤቱ የፋሲካን በግ በማረድና በመብላት መታሰቢያውን ያከብሩት ነበር (ዘፀአ.12፥1-28፤ ዘዳ.16፥1-8)፡፡ እንደዚሁም በፋሲካችን በክርስቶስ መሥዋዕት የተገኘውን ነፃነት የምናከብረው የርሱን መሥዋዕት በየጊዜው በማቅረብ ነው እንጂ እንዲያው ያለፈው ነገር እንዳይረሳ የሚደረግ እንደ እራት ግብዣ የመሰለ መታሰቢያ አይደለም፡፡

ጌታ ለመታሰቢያዬ አድርጉት ያለው ወደ እርሱ ሥጋ የተለወጠውን ኅብስትና ወደ እርሱ ደም የተለወጠውን ወይን መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ ጌታ በጸሎተ ኀሙስ ማታ ኅብስቱንና ወይኑን ባርኮና ቀድሶ ለሐዋርያት ሲሰጣቸው ይህ የሥጋዬ ምሳሌ ነው፤ ይህ የደሜ ምሳሌ ነው አላላቸውም፤ "ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት" ነው

www.eotc-mkidusan.org

ያላቸው (ሉቃ.22÷19)። እንደዚሁም "ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" ያላቸው (ማቴ.26÷28)፡፡ እንግዲህ ቅዱስ ቁርባን እንዲያው ለይምሰል የቀረበ ምሳሌያዊ መታሰቢያ ሳይሆን በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ የተሠዋው የጌታችን አማናዊ ሥጋውና አማናዊ ደሙ መሆኑን ከላይ ከተጠቀሱት ከባለቤቱ ቃል ለማረጋገጥ እንችላለን፡፡

ለመታሰቢያ ለመታሰቢያማ የድንጋይ ሐውልትስ ሊሆን ይችል የለም፡፡ ነገር ግን ሌላው አስመሳይ መታሰቢያ ሁሉ እውነተኛ መታሰቢያ ሊሆን የማይችልበት ምክንያት ጌታ ስለ መዳናችን ሲል ሰው የሆነበት የምሥጢረ ሥጋዌ ዓላማ ስለማይገለጽበትና የሥጋውና የደሙ ምሥጢር ስለማይገኝበት ነው፡፡ ከዚህም ጋር ለመንፈሳዊ ሕይወታችን መንፈሳዊ ምግብ በየጊዜው ማግኘት ይኖርብናል፡፡ ስለዚህ ምሥጢረ ቁርባን የዘላለም ሕይወት ምግብ እን ዲሆነን ጌታ ራሱ አዘጋጅቶልናል፡፡

በየጊዜው የኃጢአት ሥርየት መሥዋዕት ማቅረብ በሕገ ኦሪት የታዘዘ ነው፡፡ በኦሪት ዘመን በደል የፈጸመ ሰው ለኃጢአቱ ካሣ የሚሆነውን እንስሳ ለቤተ መቅደስ ያቀርባል፡፡ በእንስሳውም ራስ ላይ እጆቹን በመጫን በደሉንና ጥፋቱን ወደ እንስሳው ያስተላልፋል፡፡ ከዚያም እንስሳው ታርዶና ተወራርዶ ለመሥዋዕት ይቀርባል (ዘሌዋ.4)፡፡ ይህም ምሳሌ ነው፡፡ ስለ በደላችንና ስለ ኃጢአታችን ካሣ፥ ቤዛ ሆኖ በእኛ ምትክ የተሠዋልንን ክርስቶስን ያመለክተናል፡፡

ስለዚህ በየጊዜው የሚፈጸመው ሥርዓተ ቁርባን የክርስቶስ ሥጋና ደም እንደ መሆኑ መጠን ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መሥዋዕት ነው፡፡ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ከተሠዋው መሥዋዕት ጋር አንድ በመሆኑ በየጊዜው ለፈጸምነው በደል ሥርየትን የምናገኘው በምሥጢረ ቁርባን እንደሆነ እናምናለን፡፡

እንግዲህ የኦሪትን የመሥዋዕት ዓይነትና ሥርዓት ምሳሌያቸውንና ታሪ ካቸውን ለመዘርዘር ጊዜ ይወስዳል፡፡ የብሉዩ ኪዳን ሥርዓትና መሥዋዕት ሁሉ ለሐዲሱ ኪዳን ምሳሌና ጥላ ስለሆኑ፥ ሁሉም ተሽረዋል፡፡ በመሥዋዕተ ቁርባን ተተክተዋል፡፡ ዛሬ በአይሁድ ዘንድ ምኲራብ እንጂ ቤተ መቅደስ የላቸውም፥ መሥዋዕትም የላቸውም፡፡ እግዚአብሔር ባወቀ በልጁ ሊቀ ካህናትነትና መሥዋዕትነት የቤተ እሥራኤል የሆነውን ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን እንዲሆን አ ድርጓል፡፡ ስለዚህ ነው ቤተ ክርስቲያን እሥራኤል ዘነፍስ ወይም ሕዝበ እግዚአ ብሔር የምትባለው፡፡ እንግዲህ ዛሬ ለእሥራኤል ዘነፍስ የሚቀርበው መሥዋዕት የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው፡፡ ሌሎችም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን በመሥዋዕ ተ ቁርባን ይፈጸማሉ፡፡

## ለ) የአገልግሎትንና የአንድነትን ጸጋ የሚሰጡ ምሥጢራት

ምሥጢረ ክህነትና ምሥጢረ ተክሊል በአንዳንድ አመለካከት የተራራቁ መስለው ቢታዩም የሚመሳሰሉበት መንገድ አላቸው፡፡ ይኸውም ከራሳቸው አ ልፎ ለሌሎች የሚተላለፍ መንፈሳዊ አገልግሎትንና ኃላፊነትን የሚያመለክቱ ምሥጢራት በመሆናቸው ነው፡፡ ክህነትን የሚቀበል ካህን ለራሱ ጥቅም ለማግኘት ሳይሆን መንፈሳዊ አባትና መምህር ሆኖ ምእመናንን ለማገልገል እን ደሆነ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ለራሱ ብቻ መዳን ከሆነ በእምነትና በጥምቀት ያገኘው ጸጋ ይበቃው ነበር፡፡ ነገር ግን የካህን ኃላፊነቱ በሌሎች መዳን ላይ ያተኮረ ስለሆነ የካህኑ የጽድቅ ሥራ የሚለካው ለሌሎች በሚያበረክተው መን ፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ስለዚህ በመንፈሳዊ አ

www.eotc-mkidusan.org

ባትነቱ መንፈሳዊ ልጆችን ማግኘትና እነርሱንም ወደ እናት ቤተ ክርስቲያናቸው በአንድነት ሰብስቦ በትምህርት በማሳደግና በመጠበቅ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራትንም በመፈጸም ኃላፊነቱን ይወጣል፡፡

እንደዚሁም በተክሊል የሚጋቡ ሁሉ አንዱ ለሌላው የሚያስፈልገውን አገልግሎት የመስጠትና የሥጋና የመንፈስ አንድነታቸውንም የማጽናት ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከእነርሱ የሚወለዱትን ልጆች የማሳደግና የማስተማር ግዴታ አለባቸው፡፡ የክርስቲያን ቤተሰብ እንደ ቤተ ክርስቲያን ስለሚቆጠር የቤተሰቡን አባላት በፍቅርና በሥርዓት ተቆጣጥሮ ከክፉ ነገር ጠብቆ ከቁም ነገር ማድረስ በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ የሚያሰጥ ታላቅ ሥራና ኃላፊነት ነው፡፡

ስለዚህ የክህነትም ሆነ የተክሊል ምሥጢራትን የሚቀበሉ ሁሉ ለሌሎች በሚያበረክቱት አገልግሎት አንፃር በአንድ ወገን እንዲመደቡ ሆነዋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ እያንዳንዳቸውን በየተራ እንደሚከተለው በአጭሩ ለመግለጽ እንሞክራለን፡፡

## 4. ምሥጢረ ክህነት

### ትርጉም

ምሥጢረ ክህነት ማለት በእግዚአብሔርና በምእመናን መካከል ተገኝተው የእግዚአብሔርን ፈቃድና ትእዛዝ ለመፈጸምና ለማስፈጸም፥ አማኞችን ለመጠበቅ፥ ለመምከርና ለማስተማር፥ እንዲሁም ለመጸለይና ለመባረክ፥ በጠቅላላው ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ለመፈጸም እንዲችሉ ለማድረግ ለተመረጡ ሰዎች በጳጳሳት ጸሎትና አንብሮተ እድ የሚሰጥ መንፈሳዊ ማዕረግና ሥልጣንን የሚያስገኝ ከፍተኛ የጸጋ ምሥጢር ነው፡፡ "ካህን" ማለት የቃሉ ትርጉም "አገልጋይ" ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሰውን ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ መንፈሳዊ አገልግሎትን የሚያበረክቱ ካህናት በእግዚአብሔር የተሠየሙ፥ ለእርሱም ሥራ ተለይተው እርሱን የሚያገለግሉ መሆን አለባቸው፡፡

እንግዲህ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ የሰጠው ትእዛዝና ተልእኮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ተጠብቆ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲከናወን የሚያ[illegible] ሐዋርያዊ ሥልጣንና ተግባርን የሚመለከት ምሥጢር እንደሆነ እናምናለን፡፡ በምሥጢረ ክህነት አማካኝነት የሐዋርያት ሥልጣንና ኃላፊነት በአንብሮተ እድ ለሐዋርያት ተተኪዎች ለካህናት ይተላለፋል፡፡ በዚህ መሠረት የተላለፈው የክህነት ሥልጣን በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናችን ይገኛል፡፡

### የምሥጢረ ክህነት አመሠራረት

የምሥጢረ ክህነት አጀማመር በኦሪት መጻሕፍት ሰፊ መሠረት አለው፡፡ ምድረ ርስትን እጣ ገብተው እንደ ሌሎች ነገዶች ሳይወርሱ እግዚአብሔርን ርስት ያደረጉ፥ ለእርሱም አገልግሎት የተለዩ ነገደ ሌዊ ስለተባሉትና ከእነርሱም ወገን የተገኘው አሮን ሊቀ ካህናት ሆኖ ስለ መሾሙ እንደዚሁም በአጠቃላይ ስለ ክህነት የተጻፈውን የኦሪት ሕግና ሥርዓት ስንመለከት በሕገ ወንጌል ለሚፈጸመው ለምሥጢረ ክህነት እውነተኛ ታሪክና ምሳሌ መሆናቸውን እንማራለን (ዘፀ.28-30፤ ዘኍ.1፥50፤ 3፥5፤ 18፤ ኢያሱ 14፥4፤ ዕብራ.6-10)፡፡

www.eotc-mkidusan.org

ኦሪትና ነቢያትን የፈጸመው ክርስቶስ እርሱ ራሱ ሊቀ ካህናት በመሆን ምሥጢረ ክህነትን በአዲስ ሥርዓትና በአዲስ ኪዳን መሥርቶታል፡፡ ካህናተ ኦሪት የእንስሳት መሥዋዕትን ያቀርቡ ነበር፡፡ ካህናተ ወንጌል ግን እጅግ የላቀውንና የተቀደሰውን የጌታን ሥጋና ደም መሥዋዕት የሚያቀርቡ ሆነዋል፡፡

የአዲስ ኪዳን ዐቢይ ሊቀ ካህናት ክርስቶስ የክህነትን ሥራ ማለት የማጥመቅን፥ የማቊረብን፥ ኃጢአት የማስተሥረይንና የመሳሰሉትን ሥልጣን ከመስጠቱ በፊት ከብዙ ተከታዮቹ መካከል አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት መርጦ ሾሟቸዋል፡፡ ክርስቶስ ሢመተ ሐዋርያትን የፈጸመው ሌሊቱን ሲጸልይ አድሮ በ ነጋታው እንደሆነ ተጽፏል፡፡ "በነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ፥ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ፡፡ በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፥ ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ ደግሞም ሐዋርያት ብሎ ሠየማቸው" (ሉቃ.6፥12-13)፡፡

ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን የመሠረተው ከደቀ መዛሙርቱ መካከል የተወሰኑትን በመምረጥና በመሾም ነበር፡፡ በመጀመሪያ ስምዖን የተባለው የዮናን ልጅ ሲመርጠው አንተ ዐለት ነህ ማለት ጠንካራ የሃይማኖት መሠረት ነህ በማለት ስሙን ጴጥሮስ ብሎ የሠየመው ራሱ ክርስቶስ ነው፡፡ ጴጥሮስ የሚለው ቃል በግሪክኛው ዐለት ማለት ነው፡፡ በዕብራይስጡ ኬፋ ይላል (ዮሐ.1፥43)፡፡ ጴጥሮስ ብፁዕ እንደ ተባለና ቤተ ክርስቲያኑንም በእርሱ ላይ እንደሚሠራት፥ የመንግሥተ ሰማያትንም ቊልፍ እንደሚሰጠው ጌታ ተናግሯል (ማቴ.16፥16-20)፡፡ ሌሎችንም ሐዋርያት እንደዚሁ መርጦ ሠይሟቸዋል፤ የሕዝቡንም ደዌ እንዲፈውሱ፥ አጋንንትን እንዲያወጡ፥ ሙታንን እንዲያስነሡ ሥልጣን ሰጥቷቸዋል (ማቴ.10፥1-8፤18፥18)፡፡ ከዚያም ሰባ ሁለቱን አርድእት መርጦ ሾሟል (ሉቃ.10፥1-4)፡፡ ይህም ጌታ ሥልጣነ ክህነትን በየደረጃው ማቋቋሙን ያስገነዝበናል፡፡ በተለይም የትንሣኤ ዕለት ጌታችን ለሐዋርያት በመገለጥ ሥልጣ ነ ክህነትን በመንፈስ ቅድስ ኃይል ሰጥቷቸዋል፡፡ "አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው፡፡ ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፦ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፡፡ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው" (ዮሐ.20፥21-23)፡፡

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሐዋርያትን በመንፈስ ቅዱስ የሾመበት ምክንያት ክርስቶስ በደሙ የመሠረታትን ቤተ ክርስቲያን ማለት ምእመናኑን (መንጋውን) እንዲጠብቁለትና እንዲመሩለት ነው፡፡ "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ" በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ካህናት የመጨረሻ ቃሉን ሰጥቷል (የሐዋ.20፥17-28)፡፡ ይህም የሚያሳየው ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ በጳጳሳት እንደምትመራ ያስረዳናል፡፡ "ጳጳስ" ማለት የግሪክ ቃል ሲሆን፥ ትርጓሜው "የበላይ ተመልካች ባለ አደራ" ማለት ነው፤ "እንደ እግዚአብሔር መጋቢ" የሚቆጠር ነው (ቲቶ 1፥7)፡፡

## ሥልጣነ ክህነት ለትውልድ መተላለፉ

የሥልጣነ ክህነት ሹመት ለሐዋርያት ብቻ ተሰጥቶ በዚያው አልቀረም፡፡ ከላይ እንደ ጠቀስነው ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን እንደ ተደረገው ሁሉ፥ ሐዋር ያው ጳውሎስና ሌሎችም ሐዋርያት ሁሉ በየሀገሩ እየተዘዋወሩ ካስተማሩና ብዙ አማ ኞችንም ካገኙ በኋላ ምእመናኑን የሚጠብቁና የሚያገለግሉ ኤጲስ ቆጶሳትን፥ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ይሾሙላቸው ነበር፡፡ በሐዋርያት ሥራ እንደ ተጻፈው

"በየቤተ ክርስቲያኑም ሽማግሌዎችን ቀሳውስትን ከሾሙላቸው በኋላ ጸመውም ከጸለዩ በኋላ፥ ላመኑበት ለጌታ አደራ ሰጧቸው" የተባለው በርናባስና ጳውሎስ በሐዋርያዊ ጉዟቸው ከስብከተ ወንጌል ሥራቸው ጋር ማኅበረ ምእመናን ባሉበት ሁሉ ሥርዓተ ክህነትን እንዳቋቋሙ ያስረዳናል (የሐዋ.14፥21-23)። ሐዋርያትም ለእነርሱ ረዳት ሆነው በኢየሩሳሌም የምትገኘውን ቤተ ክርስቲያን እንዲያገለግሉና እንዲያስተዳድሩ ሰባት ዲያቆናትን በጸሎትና በአንብሮተ እድ ሾመዋቸዋል (የሐዋ.6፥1-6)።

የክህነት ሥርዓት ከሐዋርያት ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት ሲወርድ ሲዋረድ እስከ ዛሬይቱ ኦርቶዶክሳዊት ሐዋርያዊት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ደርሷል። ሐዋርያት ክርስቶስ የሰጣቸውን ሥልጣን ለተተኪዎቻቸው አውርሰዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ ሥልጣነ ክህነትን ለጢሞቴዎስና ለቲቶ ሰጥቷቸዋል። "በሃይማኖት ኅብረት እውነተኛ ልጄ" ብሎ ለሚጠራው ለቲቶ የቀረውን ነገር እንዲያደራጅና ከሽማግሌዎችም እየመረጠ ብቁ የሆኑትን ቀሳውስትና ኤጲስ ቆጶስ እያደረገ እንዲሾም አዞታል፤ እንዲህም ብሎታል፦

> "ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማውም እኔ አንተን እንዳዘዝሁ፤ ቀሳውስትን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ። የማይነቀፍና ያንዲት ሚስት ባል የሚሆን፥ የሚያምኑም ልጆች ያሉት፥ ስለ መዳራትም ወይም ስለ አለመታዘዝ የማይከሰስ ማንም ቢኖር ሹመው"። ከዚያም በመቀጠል ኤጲስ ቆጶስን በተመለከተ እንደሚከተለው ጽፎለታል። "ኤጲስ ቆጶስ፥ እንደ እግዚአብሔር መጋቢ፥ የማይነቀፍ ሊሆን ይገባዋልና የማይኰራ፥ የማይቆጣ፥ የማይሰክር፥ የማይጨቃጨቅ፥ ነውረኛ ረብ የማይወድ፥ ነገር ግን እንግዳ ተቀባይ፥ በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ፥ ጠንቃቃ፥ ጻድቅ፥ ቅዱስ፥ ራሱን የሚገዛ ይሁን፤ ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት ደግሞ ሊመክር ተቃዋሚዎችንም ሊወቅስ ይችል ዘንድ፥ እንደተማረው በታመነ ቃል ይጽና" (ቲቶ 1፥4-9)።

ይህ የሥርዓተ ክህነት ደንብ ዛሬም ሐዋርያዊውን ውርስ ጠብቃ ለኖረችው ቤተ ክርስቲያን መመሪያ ነው። ጌታችን እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ ብሎ ለሐዋርያት የተናገራቸው ለጊዜው ለእነርሱ ሲሆን ፍጻሜው ግን እስከ ዛሬ ድረስና እስከ ዓለም ፍጻሜም ድረስ ለምትቆየው ለሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያኑና ለአገልጋዮቿ ነው (ማቴ.28፥20)።

## ሥልጣነ ክህነት ለተመረጡት ብቻ ይሰጣል

ሥልጣነ ክህነት ለሁሉም አይሰጥም። በመጀመሪያው የጴጥሮስ መልእክት ምዕራፍ 2፥9-10፦ "እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤ እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ፤ እናንተ ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም አሁን ግን ምሕረት አግኝታችኋል።" ተብሎ የተጻፈው በክርስቶስ ክርስቲያን በወልድ ውሉድ የተባሉትና በቅብዐ ሜሮን የተቀበሉትና መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ክርስቲያኖች ሁሉ የእግዚአብሔርን በጎነትና ምሕረት ለማያምኑ ወገኖች እንደ ካህናትና መምህራን ሆነው እንዲናገሩና እንዲመሰክሩ፥ በመልካም አርአያቸውም የእግዚአብሔርን ስም እንዲያስመሰግኑ ነው እንጂ አማኞች ሁሉ ሥልጣነ ክህነት አላቸው ማለት አይደለም።

ይህን የመሰለ ቃል ለእሥራኤል ሕዝብ ተነግሯል፦ "እናንተ የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ" ተብሎ ተጽፏል (ዘፀ.19፥6)። ታዲያ የእሥራኤል ሕዝብ ሁሉ ከቤተ መቅደስ ገብቶ እንደ ሊቀ ካህናቱ እንደ አሮን መሥዋዕት ያቀርባል ማለት ነውን? እንኳን መሥዋዕት ሊያቀርቡ

ቀርቶ መቅደሱን የተዳፈሩ ሁሉ የሞት ቅጣት ደርሶባቸዋል፡፡ ክህነትን በዓመፅ ለመቀማት ያሰቡት ቆሬ፥ ዳታንና አቤሮን ከነ ተከታዮቻቸውና ከነ ቤተ ሰቦቻቸው ጋር በእግዚአብሔር መዓት ተቀሥፈዋል (ዘኁ.16፤ 2ኛዜና 26፥16-21)፡፡

እግዚአብሔር ሥልጣነ ክህነትን ለመረጣቸው ብቻ መስጠቱን ለማመልከት ከአሥራ ሁለቱ ነገድ ከተሰበሰቡት በትሮች መካከል የአሮን በትር በተአምር ለምልማ እንድታብብና እንድታፈራ አድርጓል፡፡ በክህነት ላይ ለሚያምፁ ሁሉ ምልክት ሆና እንድትጠበቅ በትረ አሮን በመቅደስ ውስጥ እን ድትቀመጥ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ አዝዟል፦ "የአሮንን በትር ወደ ምስክሩ ፊት መልስ፤ማጉረምረማቸው ከእኔ ዘንድ እንዲጠፋ እነርሱም እንዳይሞቱ ለሚያምፁብኝ ልጆች ምልክት ሆና ትጠበቅ አለው" (ዘኁ.17፥1-11)፡፡

በአዲስ ኪዳንም ሥልጣነ ክህነት ለተመረጡት ብቻ እንጂ አማኞች ለሆ ኑት ሁሉ ለወንዶችም ለሴቶችም አይሰጥም፡፡ እንዲህማ ካልሆነ ክርስቶስ ከብዙዎቹ መካከል ለምን አሥራ ሁለቱን ከዚያም ሰባውን ደቀ መዛሙርት ብቻ መረጠ? ሐዋርያው ጳውሎስም የክህነት ሹመት ከመሰጠቱ በፊት በጥንቃቄ እንዲሆን በማሰብ መልካም ጠባያቸውና አኗኗራቸውን በማስመልከት መመረጥና መሾም ስለሚገባቸው ካህናት መመሪያ አዘጋጅቷል (1ኛጢሞ.3፥1-13፤ ቲቶ 1፥6-9)፡፡ በዚህም ምክንያት ፈጥኖ እጆቹን በመጫን ካህናትን እንዳይሾም ጢሞቴዎስን አስጠንቅቆታል (1ኛጢሞ.5፥22)፡፡

ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ይህ መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን በሕገ ቤተ ክርስቲያናችን ተደንግጓል፡፡ ዲቁና ለመቀበል የሚፈልግ ሁሉ ከቃል ትምህርቱ ጋር ትምህርተ ሃይማኖትን፥ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን እና ትእዛዛትን ሁሉ በመጠኑም ቢሆን ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ከዚህም ጋር በመልካም ጠባዩና በታዛዥ ነቱ የተመሰከረለት ካልሆነ ክህነት ባይቀበል የተሻለ ነው፡፡

እንደዚሁም የቅስና ማዕረግ ለማግኘት የሚመጣ ሁሉ ስለ ሃይማኖትና ስለ ምሥጢራት ጠንቅቆ ማወቅ አለበት፡፡ በተለይም ሕገ እግዚአብሔርንና ሕገ ቤተ ክርስቲያንን አውቆ የሚያሳውቅ፥ ሕዝብን የሚያስተምርና የሚመክር የሚገሥፅም እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም ጋር የብሉያትና የሐዲሳት መጻሕፍትን ያወቀ፥ በተለይም ቅዱስ ወንጌልንና መልእክታትን ያጠና፥ በተጨማሪም ስለ መልካም ጠባዩና አኗኗሩ የተመሰከረለት ከሆነ ለሥልጣነ ክህ ነት ብቁ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህንን የትምህርት ችሎታና የጠባይ ሁኔታ ሳ ያሟሉ በግድ ክህነት ይሰጠን ማለት ለተቀባዩም ሆነ ለሰጪውም በእግዚአብሔር እና በሰው ዘንድ ከማስወቀሱም በላይ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ያልተጠበቀ ችግርን ያስከትላል፡፡ እውነተኛ ካህን ከእምነት በአፍአ ማለት ከእምነት ውጭ ያሉትን ሰዎች አስተምሮ የሚያሳምን፥ መናፍቃንን ተከራክሮ የሚረታ መሆን አለበት፡፡

## *የካህን ዐበይት ተግባራት ሦስት ናቸው*

ካህናት ሁሉ በጥንቃቄ ተመርጠው እንዲሾሙ የተባለበት ምክንያት ሥራቸውና ኃላፊነታቸው ከፍተኛ በመሆኑና የክርስቶስም አደራና ትእዛዝ ያለበት ስለሆነ ነው፡፡ ክርስቶስ ሐዋርያትን መርጦ የሾማቸው ሦስቱን ዐበይት ተግባራት እንዲፈጽሙ ነው፡፡ "ሒዱና አስተምሩ" የሚለው ትእዛዝ ትምህርተ ወንጌል ለሰው ልጆች ከሁሉ በፊት የሚያስፈልግ መሠረታዊ ነገር መሆኑን ያስረዳናል (ማቴ.28፥19-20)፡፡

www.eotc-mkidusan.org

ስለዚህ የካህን የመጀመሪያ ተግባሩ ጸሎትና ቃለ እግዚአብሔርን ለማስተማር መትጋት ነው፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያት ሌላውን ሥራ ለሌላ ሰጥተው "እኛ ግን በጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን" ያሉት (የሐዋ.ሥራ 6፥1-4)፡፡

ሁለተኛው ተግባር የሕዝቡን ኃጢአት ማስተሥረይና የቅድስናን ጐዳና ማስተማር ነው (ዮሐ.20፥23፤ 1ኛጴጥ.1፥17)፡፡ ይህም ማለት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸምና መንፈሳዊ አገልግሎትን ለምእመናን ሁሉ እንዲዳረስ ማድረግ ነው፡፡

ሦስተኛው የካህን ተግባር በጐቼን ጠብቅ፥ ግልገሎቼን አሠማራ የተባለው ትእዛዝ ነው (ዮሐ.21፥15-17)፡፡ መንጋውን የመጠበቅና የማስተዳደር ሥልጣን ለጳጳሱ ብቻ የተተወ ሳይሆን እያንዳንዱ ካህን በየአጥቢያው የሚገኙትን ምእመናን ከነጣቂ ተኩላዎች፣ ከመናፍቃንና ከከሐዲዎች እንዲሁም ዲያብሎስ ካጠመደው ከኃጢአት ወጥመድ እንዳድኑ በየጊዜው ሳይሰለቹ ማስተማርና መምከር መገሠፅና መመስከር ያስፈልጋል፡፡

ካህናት ሐዋርያዊ ተግባራቸውንና ተልእኳቸውን ለመፈጸም፥ መን ፈሳዊ አገልግሎታቸውን ለማከናወን የምእመናንን ትብብር ይጠይቃሉ፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ለሁላችንም ስለሆነና ትእዛዙንም መጠበቅ የሁላችንም ኃላፊነት ስለሆነ ምእመናን ሁሉ በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን እንዲተዳደሩና እን ዲመሩ ቤተ ክርስቲያን አደራ ትላለች፡፡

## የክህነት ማዕርጋት ሦስት ናቸው

ሐዋርያዊ ትውፊት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ሦስት የክህነት ማዕ ርጋት አሏቸው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የኤጲስ ቆጶሱ ማዕርገ ክህነት ነው፡፡ ኤ ጲስ ቆጶሱ (ጳጳሱ) በሐዋርያት ወንበር ላይ የተቀመጠ ስለሆነ ሥልጣነ ክህነቱ ምሉዕ ነው፤ አይከፈልበትም፡፡ ሐዋርያዊ ትውፊት ያለው ሐዋርያትን መስሎ፥ ሐዋርያትን አክሎ የሚሠራ፥ የክርስቶስ እንደራሴና ባለ ሙሉ ሥልጣን ስለሆ ነ በቤተ ክርስቲያን ከፍተኛውን ማዕርግ ይይዛል፡፡ ሥልጣነ ክህነት በምልዓት ከእርሱ ብቻ ስለሚገኝ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን በአንብሮተ እድ የመሾም መብትና ኃላፊነት የእርሱ ብቻ ነው፡፡ ሜሮን የመባረክ፥ አዲስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንንና ንዋያተ ቅድሳትን የመባረክ ሥልጣን የኤጲስ ቆጶሱ ነው፡፡

በክህነት ማዕረግ ሁለተኛውን ቦታ የሚይዘው ቄሱ ነው፡፡ ከኤጲስ ቆጶሱ ቀጥሎ የሚገኘው ደረጃ የቄሱ ስለሆነ ክህነት ከመስጠት በስተቀር ስድስቱንም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ይፈጽማል፡፡ ሌሎቹንም መንፈሳዊ አገልግሎቶች ያከናውናል፡፡ ለምእመናንም የወንጌል ትምህርትና ምክር መስጠት መብቱና ግዴታው ነው፡፡ ለምእመናንም አበ ነፍስ በመሆን በመንፈሳዊ አባትነቱ መን ፈሳዊ ልጆቹን ይጠብቃል፤ የችግራቸውም የኀዘናቸውም ተካፋይ ይሆናል፡፡

በሦስተኛ ማዕርገ ክህነት ተመድቦ የሚገኘው ዲያቆኑ ነው፡፡ እርሱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ለመፈጸም መብት ባይኖረውም ቄሱና ኤጲስ ቆጳ ሱ ምሥጢራቱን በሚፈጽሙበት ጊዜ በመርዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥርዓትን መጠበቅ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ፥ ማስተማርና መስበክ፥ ሌሎችንም መንፈሳዊ አገልግሎት መፈጸምና ለጳጳሱና ለቄሱ መታዘዝ የዲያቆኑ የሥራ ድርሻ ይሆናል፡፡ ሐዋርያት ሰባቱን ዲያቆናት የሾሙበት ዋና ምክንያት በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ለሚያስፈልገው መንፈሳዊና

www.eotc-mkidusan.org

ማኅበራዊ አገልግሎት እንዲረዱዋቸው መሆኑን እናስታውሳለን (የሐዋ.6፥3-6)።

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተጨማሪ የሴት አገልጋዮች ዲያቆናውያት የተባሉ እንደነበሩ ተጽፏል (ቲቶ 2፥3፤ ዲድስቅልያ 34)። እነርሱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተወሰነ ሥራ ነበራቸው። ለሴቶች ክርስቲያኖች ለምእመናት አገልግሎት በመስጠት፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሴቶች መቆሚያ በኩል ተገኝተው ሥርዓትን በመጠበቅና በማስተናበር፥ በመምከርና በመርዳት፥ ጉዳይ ያላቸውንም ሴቶች ወደ ቄሱና ጳጳሱ በማቅረብና ለችግራቸውም መፍትሔ ማስገኘትና ሌሎችም የመሳሰሉትን መንፈሳዊ ተግባራት ይፈጽማሉ። ከዚህም በላይ ሴቶች በሚጠመቁ ጊዜ ቅዱስ ሜሮንን በመቀባት ይረዱ ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ እድሜያቸው ከስድሳ ዓመት ያላነሰ ሴቶች በቤተ ክርስቲያን እንዲመዘገቡ የፈቀደው ስለ ዲያቆናውያትም ጭምር እንደሆነ ይታመናል (1ኛጢሞ.5፥9)።

## ምእመናንን እንዲያገለግል ለካህኑ የተሰጠው ጸጋ ታላቅ ነው

ምሥጢረ ክህነት ሲፈጸም የሚታየውና የሚደረገው ነገር የጳጳሱ አንብሮተ እድና የጸሎቱ ሥነ ሥርዓት ነው። በዚህ ሥርዓት ማለት በጳጳሱ አማካኝነት ደግሞ እግዚአብሔር የማይታየውን ጸጋ ለካህኑ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይሰጠዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ አንብሮተ እድ የጻፈው ነገር የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታ ያሳስበናል። "እሳት እንደሚያቀጣጥል ሰው፥ እጆቼን በመጫኔ በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሣሣ አሳስብሃለሁ" (2ኛጢሞ.1፥6፤ 1ኛጢሞ.4፥14)። ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ የማይታይ ጸጋ ሲሆን፥ የካህኑን ሥልጣንና ተግባር የሚያስፈጽምለት፥ ለምእመናን የሚያበረክተውን አገልግሎት የሚያሠምርለት የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ረድኤት ታላቅ ነው።

በዚህ ምሥጢር አማካኝነት ክርስቶስን ወክለው እንደ ሐዋርያት ሥልጣን አግኝተው ሦስቱን ምግባራት ለማከናወን የሚያስችል ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ። እንደ ክርስቶስ ነቢይ፥ ካህንና ንጉሥ ሆነው የእርሱን ቤተ ክርስቲያን እንዲያገለግሉ ጸጋ ተሰጥቷቸዋል ማለት ነው። እንደ ነቢይ ወንጌልን የማስተማር፥ እንደ ካህን ኃጢአትን የማስተሥረይ፥ እንደ ንጉሥ መንጋውን የመጠበቅና የማስተዳደር ሥልጣን አላቸው። ስለዚህም ክርስቶስን የሚያስመስላቸው ታላቅ የጸጋ ስጦታን እንዳገኙ እናምናለን።

የክህነት ሥርዓት ለካህናት መጠቀሚያ የሚመስላቸው ቢኖሩ ተሳስተዋል። እግዚአብሔር ሥራውን ለመሥራትና ሰዎችን ለማዳን ሲፈልግ በሰዎች አማካኝነት ይሠራል። በጥንት ጊዜ እግዚአብሔር ነቢያትን በመላክ ፈቃዱን ይገልጻል፤ ትእዛዛቱን ያስከብራል። በኋለኛውም ዘመን ክርስቶስ ሰው በመሆን ስለ ሰዎች መዳን ሲል ራሱን ካህን ራሱን መሥዋዕት አድርጐ ዓለምን አድኗል፤ ሥራውንም ፈጽሞ ከሰማያዊ ስፍራው ተመልሷል። ይህንን የማዳን ሥራውን፥የምሥራቹን ዜና ለሕዝብ የሚያደርሱ መልእክተኞች በግድ ያስፈልጋሉ። ያለ መልእክተኛ መልእክቱ ከግቡ አይደርስምና። ሐዋርያት ማለትም ልዑካን መልእክተኞች ማለት ነው።

ስለዚህ የመዳኑን መልእክት ለሕዝቡ ለማድረስ የምእመናኑንም ኃጢአት ለማስተሥረይ ሐዋርያትንና አርድእትን፥ ካህናት እንዲሆኑ ማለት እንዲያገለግሉ መርጦ የሾማቸው ራሱ ክርስቶስ ነው። ይህንንም ያደረገው ለምእመናን መጠቀሚያ፥ ለኃጢአታቸው ማስተሥረያና ከእግዚአብሔር መታረቂያ እንዲሆን በማሰብ ነው። በተሰጣቸውም የአገልግሎት ጸጋ ሰውን ከእግዚአብሔር ያስታርቃሉ (2ኛቆሮ.5፥18-21)። ስለዚህ የዛሬዎቹ ካህናትም ሐዋርያትን

www.eotc-mkidusan.org

በመተካት በተሰጣቸው ሐዋርያዊ ጸጋ ምእመናንን እንዲያገለግሉ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ረድኤት እንደማይለያቸው የቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው ክርስቶስ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ ያለው ቃል ሕያው ምስክር ሆኖ ለዘላለም ይኖራል (ማቴ.28፥20)።

## 5. ምሥጢረ ተክሊል

### ትርጉሙና አመሠራረቱ

ምሥጢረ ተክሊል ማለት የሙሽራውና የሙሽራይቱን የጋብቻ ቃል ኪዳን በሃይማኖት የሚያጸና፥ የጋብቻ ግዴታን ለመወጣት የሚያስችል፥ በፍቅር የሚያስተሣሥር፥ ዘላቂ አንድነትን የሚያስገኝ ከቅዱስ ቁርባን ጋር የሚሰጥ የጸጋ ምሥጢር ነው። ቅዱስ ጋብቻ ለክርስቶስና ለቤተ ክርስቲያን ፍቅርና አን ድነት ምሳሌ ስለሆነ ታላቅ ምሥጢር መሆኑን ያስረዳናል (ኤፌ.5፥31-32)። ጌታችንም በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት ተገኝቶ ውኃውን ወደ ወይን ለውጦ ለሙሽሮቹና ለሠርገኞቹ ሁሉ መስጠቱ በደሙ የዋጃትን የሙሽራይቱ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ሆኖ ይተረጐማል (ዮሐ.2፥1-11)። በተአምር የተገኘው ወይን በጸሎተ ኀሙስ ማታ ጌታ የባረከውን ጽዋ ያመለክተናል። ስለዚህ የተክሊል ወይም የእውነተኛ ጋብቻ ምሥጢር ከቅዱስ ቁርባን ጋር የተያያዘ ስለሆ ነ ያለቁርባን የሚፈጸም ተክሊል መንፈሳዊ ትርጉም የለውም።

ከላይ እንደ ተጠቀሰው ጌታችን ከቅድስት እናቱ ከድንግል ማርያምና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በሠርግ ቤት በመገኘት በእመቤታችን አማላጅነት ተአ ምራቱን በመግለጽ፥ ሠርጉን በመሳተፍ፥ የታደሉትን ሙሽራና ሙሽሪት በመባ ረክ የቅዱስ ጋብቻን ምሥጢር ከሁሉ በሚቀድመው ተአምራቱ መሥርቶታል። ይህም በኋላ ጊዜ ጌታ በአዲስ ኪዳን በደሙ ለሚመሠርታት ቤተ ክርስቲያን ለእውነተኛው ቃል ኪዳንና አንድነት ማስረጃ እንዲሆነው በሠርጉ ሥነ ሥርዓት ተገኝቶ የደሙ ምልክት የሆነውን መልካሙን ወይን አስገኝቶላቸዋል። ስለዚህም በቅዱስ ጋብቻ ተመሥርተው የሚኖሩ ሙሽሮች የተቀደሱ አባትና እናት ይሆናሉ።

ከተቀደሱ ወላጆችም የሚያምኑና የተጠመቁ ልጆች የቤተሰብ አባሎች ይፈጠራሉ። የሚያምኑ ቤተሰቦችም የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አካላትና አባላት ይሆናሉ። ስለዚህ ቅዱስ ጋብቻ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙነት ምሳ ሌያዊ ብቻ ሳይሆን እውነተኛና መሠረታዊ ሁኔታ እንዳለው እንገነዘባለን። ይህም ማለት ቅዱስ ጋብቻ ለእውነተኞቹ የቤተ ክርስቲያን አባላት ብዛትና ጥራት፥ እድገትና መሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል ማለት ነው።

ከሥነ ፍጥረት ጀምሮ ቅዱስ ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት ብቻ ተመሥርቶ የሚፈጸም መሆኑን ጌታችን አስተምሯል። "ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል" በማለት አስረድቷል (ማቴ.5፥32)። የፍቺውን ደብ ዳቤ ከሰጣት በኋላ ባል ሚስቱን ለመፍታት ይችላል በማለት ሙሴ የፈቀደበት ምክንያት ምን እንደሆነ ጌታ ተጠይቆ መልስ ሲሰጥ ሙሴ ይህን ያደረገው ስለ ልባቸው ክፋት እንደሆነ ገልጾ አስረድቷቸዋል። ከጥንት ግን አንድ ወንድና አን ዲት ሴት ብቻ ነበሩ። እነርሱም "አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለ

የውም" (ማቴ.19፥1-9፤ ዘፍ.1፥27፤ 2፥24፤ ዘዳ.24፥1)፡፡ ስለዚህ ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት ብቻ የተመሠረተና መፋታትም የተከለከለ መሆኑን ከቅዱስ ወንጌል ተምረናል፡፡

ልዩ ስጦታ ካላቸው ጥቂት ሰዎች በስተቀር ማንኛውም ክርስቲያን የቅዱስ ጋብቻን ሥርዓት መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ጋብቻ አያስፈልገኝም ብሎ ለብቻ በንጽሕና በድንግልና መኖር ለሁሉም ሰው እንደማይቻል በወንጌል ተጽፏል፡፡ ባልና ሚስት ሳይፋቱ መኖር እንዳለባቸው ጌታ ስለ አስተማረ ደቀ መዛሙርቱ፦ "የባልና የሚስት ሥርዓት እንዲህ ከሆነ መጋባት አይጠቅምም አሉት፡፡ እርሱ ግን፦ ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም፤ በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፥ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፥ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ፡፡ ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው አላቸው" (ማቴ.19፥10-12)፡፡ እንግዲህ ከዚህ እንደ ተገለጸው ከጥቂቶች ማለት ከሕፀዋን፥ ከደናግልና ከመነኮሳት በስተቀር ሁሉም በጋብቻ ሕግ መኖር እንዳለበት ያስገነዝበናል፡፡

## *የጋብቻ ዓላማና ጥቅም*

ጋብቻ በእግዚአብሔር የታዘዘ የተፈጥሮ ሕግ ቢሆንም ዋናው ዓላማው ልጆችን ለመተካት የሰው ዘርን ለማብዛት መሆኑ የተጻፈ ነው (ዘፍ.1፥27-28)፡፡ እግዚአብሔር እንደ መላእክት የመጀመሪያውን ሰው አዳምን በዘር በልደት አልፈጠረውም፡፡ ከአዳምና ከሔዋን በኋላ የተፈጠሩት ሰዎች ግን በዘር በሩካቤ የተገኙ ስለሆነ ወላጆች ልጆችን በማስገኘት የሰው ዘር በምድር ላይ እንዲበዛ በማድረግ የእግዚአብሔር ሥራ ተባባሪዎች ናቸው፡፡ ስለዚህም ወላጆች በኅብረተሰቡ ዘንድ የተከበሩ እንዲሆኑ ከአሠርቱ ትእዛዛት አንዱ ስለ እነርሱ ክብር የታዘዘ ነው (ዘፍ.20፥12)፡፡ ወላጆችም ከዚህ ክብር የደረሱት ቅዱስ ጋብቻን በማክበራቸው ነው፡፡ ጋብቻቸውን በምሥጢረ ተክሊል የፈጸሙ እስከ መጨረሻውም በቅዱስ ቁርባን የጸኑ አባትና እናት ክብራቸው እጥፍ ድርብ ነው፡፡ በምድርም በሰማይም የተመሰገኑ ናቸው፡፡

ሁለተኛው የጋብቻ ዓላማና ጥቅም እርስ በእርስ መረዳዳት ነው፡፡ "እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት" በማለት ሔዋንን ፈጠረ፡፡ ሁለቱም እየተረዳዱ እንዲኖሩ ሆነዋል (ዘፍ.2፥18-25)፡፡ ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ እንዲሉ፥ ዛሬም ብዙ የክርስቲያን ቤተሰቦች በቅዱስ ጋብቻ በመጽናት፥ የእግዚአብሔርን ረድኤት በማግኘት እርስ በእርሳቸው በመተባበርና በመረዳዳት ኑሯቸውን አቸንፈው የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ ፈጽመው መገኘታቸው ሁላችንንም ያስደስተናል፡፡ እንግዲህ ጋብቻን ያልመሠረቱት ሁሉ የእነዚህ ዓይነት ቤተሰቦችን አርአያ እንዲከተሉ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች፡፡

የጋብቻ ሦስተኛው ዓላማና ጥቅሙ ከአመንዝራነት ለመዳንና የሥጋ ፍትወትን ለመቆጣጠር እንደሆነ ይታመናል (1ኛቆሮ.7፥8-9፤ ማቴ.19፥10-12)፡፡ ከዚህም ሌላ በዝሙት ጠንቅ ከሚመጣው የሥጋ ደዌና የመንፈስ ጭንቀት፥ የቤተሰብ ችግርም የሚዳነው የቅዱስ ጋብቻን ዓላማ በመጠበቅ ነው፡፡ በተለይም በዘመናችን በተከሠተው ችግር ምክንያት አንድ ወንድ በአንዲት ሴት፥ አንዲት ሴት በአንድ ወንድ እንዲጸኑ ክርስቲያን ያልሆኑት ሁሉ የሚያስተምሩበት ዐቢይ ርእስ ሆኗል፡፡ እንግዲህ ሁላችንም የጋብቻ ዓላማና ጥቅም ትልቅ መሆኑን አውቀን ማሳወቅ፥ ጠብቀን ማስጠበቅ ለኅብረሰተቡም አርአያ መሆን ይገባናል፡፡ በቅዱስ ጋብቻ መጽናት በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋን

www.eotc-mkidusan.org

ያሰጣል፤ በሰውም ዘንድ ያስከብራል፤ ለቤተሰቡ ሁሉ ጤንነትንና ሰላምን ያስገኛል፡፡

## የምሥጢረ ተክሊል ጸጋ

ከላይ እንደ ተጠቀሰው ምሥጢረ ተክሊልን ከቅዱስ ቁርባን ጋር በመፈጸም የማይታየውን ታላቁን የእግዚአብሔር ጸጋ እንቀበላለን፡፡ ከሥጋዊ አንድነት በላይ የሚሆነውን የመንፈስ አንድነትና ፍቅርን በተጠናከረ ሁኔታ እናገኛለን፡፡ በተክሊል የምናገኘው ጸጋ ጋብቻችንን የተከበረና መንፈሳ ችንንም የተቀደሰ ያደርገዋል፡፡ "መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር፥ መኝታውም ን ጹሕ ይሁን" የተባለውን ለመፈጸም ያስችለናል (ዕብ.13፥4)፡፡ እንግዲህ ይህን የተሰጠውን የአንድነት ጸጋ ዘላቂ ለማድረግና የእግዚአብሔርን ረድኤት ለማብዛት በየጊዜው ሁለቱም በአንድነት መቊረብና በአንድነት የኅብረትና የቤተ ሰብ ጸሎት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም ጋር ቃለ እግዚአብሔርን በመስማት ለሕይወታቸው የሚያስፈልገውን መንፈሳዊ ምግብ ያገኛሉ፡፡

የነፍስ አባትንም በማቅረብ ችግር ቢኖርም ባይኖርም ስለ ኑሮ ሁኔታ ተገላልጦ መወያየትና ከመምህረ ንስሐቸውም ምክርና ትምህርት፥ ጸሎትና ቡራኬን መቀበል እጅግ ይጠቅማል፡፡ እንደዚህ የሚያደርጉ ቤተሰቦች መንፈሳዊ ኃይልን ያገኛሉ፥ የጋብቻ ሕይወታቸው ይታደሳል፥ ሥጋዊና መንፈሳዊ አንድ ነታቸው ይጸናል፡፡

እንግዲህ የጋብቻን ግዴታ ለመወጣት፥ ልጆችን በክርስቲያናዊ ሥርዓ ት አሳድጎና አስተምሮ ለወግ ለማዕረግ ለማብቃት፥ ጊዜያዊ የኑሮ ችግሮችን ለመቋቋም፥ የሚያጋጥመንንም የቤተሰብ ፈተና ለማለፍ ከራስ ጥረት ጋር በእግዚአብሔር ረድኤት መተማመን ነው፡፡ በተለይም አንዱ የሌላውን ሸክም ተሸክሞ፥ አንዱ የሌላውን ጉድለት ችሎና ተቻችሎ እስከ ሞት ድረስ በትዕ ግሥት በመኖር፥ ፍቅርን እስከ መቃብር ለማድረስ መንፈሳዊ ተጋድሎ የሚያደርጉ ቤተሰቦች ብፁዓን ናቸው፤ ከእግዚአብሔርም የማያልፈውን ተድላና ደስታ ያገኛሉ፡፡

የምሥጢረ ተክሊልም ዓላማና ፍጻሜ ወላጆች በቅዱስ ቁርባን ጸንተው የዘላለም ሕይወትን ጸጋ እንዲቀዳጁ ለማድረግ ነው፡፡ ተክሊል ሲፈጽሙ ቤተ ክርስቲያን ያደረገችላቸውን አክሊል አክብረው በመጠበቅ፥ የትዳርንም ውጣ ውረድ በትዕግሥት በመቻል እስከ መጨረሻው ለኑሮ ጓደኞቻቸውና ለእግዚአ ብሔር ታማኝነታቸውን ካስመሰከሩ የሰማያዊውን የሕይወት አክሊል ይቀበላሉ፡፡

## ሐ) የነፍስና የሥጋ ፈውስ የሚገኝባቸው ምሥጢራት

እስከ አሁን የተመለከትናቸው ሦስቱ ምሥጢራት ጥምቀት፥ ሜሮንና ቁርባን በአንድ ወገን ተቆጥረው ስለ መጀመሪያውና መሠረታዊው የክርስቲያን ሕይወታችን ያስረዱናል፡፡ ከውኃና ከመንፈስ በመወለድ አዲስ ሕይወት እን ድናገኝ፥ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እንድንጠናከር፥ መንፈሳዊ ምግብ በመብላት እን ድናድግና ወደ ሙሉ ክርስቲያናዊ ሕይወት እንድንደርስ ያበቁናል፡፡ ከእነርሱ የሚገኘው ጸጋና ረድኤት መለኮታዊ ባሕርዩን ክብሩን ለመሳተፍ እንድንችል እድል ይሰጡናል፡፡ የኛን ፈቃድ በማነሣሣትና በማስተባበር የተሰጡን የጸጋ ስጦ ታዎች ራሳችንን ከክፉ ነገር እንድንጠብቅና የተቀደሰውንም ሕይወት እንድንኖር ያስችሉናል፡፡

ዳሩ ግን በዚህ በክፋትና በበደል በተያዘ ዓለም ውስጥ የምንኖር ስለሆነ የተ ሰጠንን ጸጋ እንድንተውና ከብዙ መከራና ፈተና ውስጥ እንድንወድቅ የሚሆን

www.eotc-mkidusan.org

በት ጊዜ አለ፡፡ ከሥጋዊ ፈቃዳችንና ከምድራዊ ኑሯችን ውሱንነትና ደካማነት የተነሣ የሚያጋጥሙን የክፋት ኃይሎች መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወታችንን በማጕሳቆል ለልዩ ልዩ ሕማምና አደጋ ይዳርጉታል፡፡ የሰው ልጆች ኑሮ ለልዩ ልዩ ኃጢአትና በደል፥ ለሕማምና ደዌ፥ ለጭንቀትና ለሥቃይ የተጋለጠ መሆኑን የሚያውቅ ቸርና መሐሪ የሆነው አምላካችንና መድኃኒታችን ለነፍሳችንና ለሥጋችን ቁስል መጠገኛ የሚሆነውን የፈውስና የመዳን ምሥጢራትን በቅድሚያ አዘጋጅቶልናል፡፡ እነርሱም ለነፍሳችን ቁስል መዳኛ ምሥጢረ ንስሐ፥ ለሥጋችን ደግሞ ምሥጢረ ቀንዲል ስለሆኑ ስለ እነርሱ እንደሚከተለው ልናውቀው የሚገባንን ያህል በመጠኑ እንገልጻለን፡፡

## 6 ምሥጢረ ንስሐ

### የንስሐ አስፈላጊነትና ምንነት

ምሥጢረ ንስሐ ማለት ምን ማለት መሆኑን ለማወቅ በቅድሚያ አስፈላጊነቱን ብንመለከት ወደ ፍሬ ነገሩ ለመድረስ ይረዳናል፡፡ እንደ ታዘብነው ጥቂት ክርስቲያኖች ከተጠመቁና ከቆረቡ በኋላ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ፥ ለቀላልም ሆነ ለከባድ ኃጢአት ተጋልጠው በጨለማ ውስጥ ሲመላለሱ እናያቸዋለን፡፡ ቁጥራቸው አይብዛ እንጂ አንዳንዶቹማ በስመ ክርስቲያን ከባድ ወንጀል በመፈጸም በኃጢአት አዘቅት ውስጥ ወድቀው ይገኛሉ፡፡ ሁኔታውን በጽሞና ለተመለከተው ሐቀኛ ክርስቲያን ሁሉ ጉዳዩ እጅግ ያሳዝናል፡፡ ነገር ግን እንዲህ ያለው ሁኔታ ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ የነበረ ነው፡፡ ለምሳሌ በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መካከል ከነበሩት አንዱ ስሙ ያልተጠቀሰ ሰው ከፍተኛ የዝሙት ኃጢአት እንደ ፈጸመና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም እንደገሠፀው እናነባለን (1ኛቆሮ.5፥1-13)፡፡

እንዲሁም ደግሞ ክርስቲያን ከክርስቲያን ወንድሙ ጋር ተጣልቶ ወደ ኢአማንያን ፍርድ ቤት ተያይዘው በመሄዳቸው ቅሬታውን፥ ትምህርቱንና ምክሩን ይኸው ሐዋርያ በጻፈው መልእክቱ ገልጾታል (1ኛቆሮ.6፥1-11)፡፡ የሐዋርያው ጳውሎስ ረዳት የነበረ ዴማስ የተባለ ደቀ መዝሙር ይህን ዓለም በመውደዱ ሐዋርያውን ትቶት ሄዷል (2ኛጢሞ.4፥10)፡፡ ይህን የመሰለ ታሪክ በብሉይም በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትም ይገኛል፡፡

ለጌታ ክብር ምስጋና ይግባውና የሰውን መመለስ እንጂ ጥፋቱን የማይወድ አምላክ የምንመለስበትን የንስሐ መንገድ አዘጋጅቶልናል፡፡ ከአዳም የወረስነው በኃጢአት የጐሰቆለ ሰውነት ደካማ በመሆኑና በክፉ ምኞቱም እየተነዳ ሰውን ወደ ጥፋት ጐዳና የሚጐትተውና የሚጥለው ስለሆነ በጸጋ እግዚአብሔር ካልተረዳ በስተቀር ከጥፋት አዘቅት ውስጥ ወድቆ ይቀራል፡፡ ስለዚህ ለመነሣት የሚረዳውና ለደኅንነቱ የሚያስፈልገው ምሥጢረ ንስሐ በቅድሚያ ተዘጋጅቶለታል፡፡

እንግዲህ ምሥጢረ ንስሐ ማለት አንድ ሰው ከጥምቀት በኋላ የፈጸመውን ጥፋት አውቆ ሁለተኛ ጥፋትን ላለመድገም ወስኖ በእግዚአብሔርና በካህኑ ፊት ተንበርክኮ በልቡ ተፀፅቶ ኃጢአቱን በመናዘዝ ከኃጢአቱ እሥራት የሚፈታበትና ከእግዚአብሔር ይቅርታን የሚያገኝበት ታላቅ የጸጋ ምሥጢር ነው፡፡ "ከጥምቀት በኋላ" የተባለውም በጥምቀቱ ጊዜ ከአዳም የወረሰውን እርሱም የሠራው ኃጢአት ሁሉ የተሠረየለት ስለሆነ ነው፡፡

www.eotc-mkidusan.org

## *የምሥጢረ ንስሐ አመሠራረት*

ምሥጢረ ንስሐን የመሠረተ ራሱ ጌታችን ነው፡፡ ለሰው ልጆች አዛኝ የሆነው መፍቀሬ ሰብእ ክርስቶስ የኛን ኃጢአት ሁሉ በሰውነቱ ተሸክሞ በሕማምና በሞቱ አንድ ጊዜ አድኖናል፡፡ ይህንንም ጸጋ በምሥጢረ ጥምቀት አግኝተነዋል፡፡ ከዚያም በኋላ ለምንፈጽመው በደል ማስተሥረያ እንዲሆነን፥ ለሐዋርያቱና እነርሱንም ለሚተኩት ካህናት ሥልጣንን በመስጠት ምሥጢረ ንስሐን መሥርቶልናል፡፡ ኃጢአትን የማስተሥረይ ሥልጣን የእግዚአብሔር ብቻ ሲሆን፥ ለእኛ ጥቅምና ደኅንነት ሲል ይህን ሥልጣን ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ለጴጥሮስና ለሐዋርያት ተከታዮች ሰጥቷል፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ እውነተኛው እምነት ከመሰከረ በኋላ ሥልጣነ ክህነትን ማለት የመንግሥተ ሰማያትን ቁልፍ ክርስቶስ ሰጥቶታል፡፡ እንዲህም ብሎታል፦ "የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ በምድር የምታሥረው ሁሉ በሰማያት የታሠረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል" (ማቴ.16፥19)፡፡

እንደዚሁም ይህን ሥልጣን ለሌሎች ሐዋርያት ሰጥቷቸዋል፡፡ " እውነት እላችኋለሁ፥ በምድር የምታሥሩት ሁሉ በሰማይ የታሠረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል" (ማቴ.18፥18)፡፡ ከትንሣኤው በኋላም የትንሣኤ ዕለት ለሦስተኛ ጊዜ ኃጢአት የማስተሥረይ ሥልጣን ሰጥቶ በመንፈስ ቅዱስ ስጦታ አረጋግጠላቸዋል፥ አትሞላቸዋል፡፡ "አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው፡፡ ይህንንም ብሎ እፍ አለባቸውና፦ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፡፡ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው" (ዮሐ.20፥21-23)፡፡

እንግዲህ ኃጢአትን የማስተሥረይ ሥልጣን ለእነርሱ የተሰጠ ስለሆነ በሐዋርያት እግር ለተተኩት ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ለካህናት ኃጢአታችንን ከመናዘዝ ቸል አንበል፡፡ የአንዳንድ ችግረኞች ካህናትንም ሁኔታ በማየት በንቀት ዓይን ማየቱን እንተው፡፡ ይህ የዓለማዊ ሰዎች አጉል ስሜታዊ አመለካከት ስለሆነ ከዚህ እንራቅ፡፡ ይልቅስ ሥልጣንን የሰጣቸውን እግዚአብሔርን አምነን፥ በትኅትና መንፈስ ሆነን ኃጢአታችንን ሥልጣነ ክህነት ላላቸው ቀሳውስት ተናዝዘን የኃጢአትን ሥርየት ማግኘት ታላቅ ጸጋ መሆኑን ተረድተን የምሥጢረ ንስሐን ሥርዓት መፈጸም ይጠቅመናል፡፡ ከራሳችን ሐሳብና ስሜት ይልቅ ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ ይበልጣል፡፡

## *በኃጢአት ሥርየት አምኖ ንስሐ መግባት*

ንስሐ የሚገባ ሰው በቅድሚያ ንስሐ በመግባት ኃጢአት ሁሉ እንደሚሠረይና እንደሚደመሰስ ማመን አለበት፡፡ "ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም" ተብሎ ተጽፏልና (የሐዋ.ሥራ 3፥19)፡፡ እግዚአብሔር ንስሐ በሚገቡ ሰዎች ደስ ይለዋል፡፡ ክርስቶስ ኃጥአንን እንጂ ጻድቃንን ለመጥራት እንዳልመጣ እርሱ ራሱ ተናግሯል (ማቴ.9፥13)፡፡ እውነተኛው ጠባቂያችን እረኛችን ክርስቶስ ዘጠና ዘጠኙን በጐች ትቶ የጠፋችውን አንዲት በግ እንደ ፈለጋትና ባገኛትም ጊዜ በጫንቃው ተሸክሞ ወደ ቤቱ እንዳመጣትና ታላቅ ደስታም እንዳደረገ በምሳሌ አስረድቶናል፡፡ እንዲህም አለ፦ "ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል" (ሉቃ.15፥1-7)፡፡ የአንድ ኃጢአተኛ መመለስ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ታላቅ ደስታን ያስከትላል (ሉቃ.15፥10)፡፡ እንግዲህ እግዚአብሔር ንስሐ የሚያስፈልገንን እኛን ኃጢአተኞችን ለመቀበልና ይቅር ለማለት ምን ያህል ደስ እንደሚለው መዘንጋት የለብንም፡፡ እርሱ

ጌታችን መፍቀሬ ንስሐ ከባቴ አበሳ፥ ተወካፌ ንስሐ ወሠራዬ ኃጢአት መሆኑን ማመን ይኖርብናል፡፡

አንድ ንስሐ የሚያስፈልገው ሰው በደሌ ብዙ ነው ከእግዚአብሔር ይቅርታን አላገኝም በማለት ያለንስሐ ዝም ብሎ መቀመጥ በገዛ ፈቃዱ ከቀቢጸ ተስፋ ጉድጓድ ውስጥ እንደ መውደቅ ስለሚቆጠር በነፍሱ ላይ የሚያስከትለው አደጋ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ለሰው ልጆች የማይሠረይ ኃጢአት አንድ ብቻ ነው፤ ሌሎች ኃጢአቶች ሁሉ ምንም ከባድ ወንጀሎች ቢሆኑም እንኳ ይሠረያሉ፡፡

"ስለዚህ እላችኋላሁ፥ ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ለሰዎች ይሠረይላቸዋል፥ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ አይሠረይለትም፡፡ በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሠረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሠረይለትም" (ማቴ.12፥31-32)፡፡ይህም ማለት የእግዚአብሔርን ፍቅር ማቃለል፥ የክርስቶስን የማዳን ሥራ መቃወም፥ የመንፈስ ቅዱስን የምሕረትና የይቅርታ ጸጋ መሳደብ ስለሆነ ዲያብሎስ ከፈጸመው ኃጢአት እጅግ የከፋ መሆኑን መናገር ነው፡፡ ለእንዲህ ዓይነቱ ኃጢአት ሥርየት የለም፡፡ ከዚህ ከተጠቀሰው በስተቀር ለማናቸውም በደል ይቅርታ ይደረጋል፡፡ በሰው ልጅ ላይ እንኳ ቃል የሚናገር ይሠረይለታል ተብሏልና፡፡

እንግዲህ ኃጢአታችሁ ምንም ከባድ ቢሆን ሥርየትን እንደምታገኙና ከበደላችሁም እንደምትነጹ አምናችሁ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አለባችሁ፡፡ "ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነፃለች፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች (ኢሳ.1፥18)፡፡ ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል ይነሣልም የተባለውን እያስታወስን በቀቢጸ ተስፋ የወደቀውን ስሜታችንን በማነሣሣት፥ በአጉል አስተሳሰብ የፈዘዘውን አእምሮአችንን በማነቃቃት፥ በክፉ ልማዳችን የደነዘዘውን ጉልበታችንን በማበረታታት ንስሐ ለመግባት መዘጋጀት ይኖርብናል (ምሳሌ. 24፥16፤ ዕብ.12፥12-17)፡፡

## ንስሐ በሦስት ነገሮች ይፈጸማል

እንግዲህ ንስሐ ገብተን፥ የኃጢአት ሥርየት አግኝተን፥ ከሰውና ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀን፥ በጽድቅ ጐዳና ለመራመድና በደኅንነት ጸጋ ለመኖር እንድንችል ቢያንስ ሦስት ነገሮችን መፈጸም አለብን፡፡ በመጀመሪያ የንስሐ ኀዘን ማለት እውነተኛና ልባዊ ጸጸት በቅድሚያ እንዲኖረን ያስፈልጋል፡፡ ሁለተኛው ኑዛዜ ሲሆን፥ ሦስተኛው ደግሞ ስለኃጢአታችን የሚሰጠንን የንስሐ ቅጣት የሚመለከት የቀኖናን ሥርዓት መፈጸምና እንደዚሁም በካህኑ በኩል የምናገኘው የፍትሐት ጸጋ ነው፡፡

## የንስሐ ኀዘን

ንስሐ የሚገባ ሰው በመጀመሪያ ኃጢአቱን እያስታወሰ፥ ሰውንና ፈጣሪውን መበደሉን እያሰበ የሚያደርገው ኀዘን ወደ ንስሐ የሚወስድ እውነተኛ ኀዘን ስለሆነ ኀዘኑን እግዚአብሔር ይቆጥርለታል፡፡ "የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፥ መጽናናትን ያገኛሉና" የተባለው የራሳቸውንና የሌላውን ኃጢአት እያሰቡ የሚያዝኑትን ተነሣሒያን ያመለክታል (ማቴ.5፥4)፡፡ ንሥሐ ማለት ፀፀትን የሚያመለክት ቢሆንም ቁጭትና ቅንዓት የሞላበት የዓለማዊ ፀፀት ሳይሆን እውነተኛው ኀዘንና መመለስ መሆኑን በቅድሚያ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

www.eotc-mkidusan.org

ስለ እውነተኛው ኀዘን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚከተለው ያስተምረናል፡፡ “አሁን ለንስሐ ስላዘናችሁ ደስ ብሎኛል እንጂ ስላዘናችሁ አይደለም፤ በምንም ከእኛ የተነሣ እንዳትጐዱ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አዝናችኋልና፡፡ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኀዘን ፀፀት የሌለበትን፥ ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንስሐ ያደርጋልና፤ የዓለም ኀዘን ግን ሞትን ያመጣል” (2ኛቆሮ.7፥9-10)፡፡ እንግዲህ እውነተኛውን ኀዘን ከእንባው ጋር አድርጐ በንጹሕ ልቡናና ጸሎት ለእግዚአብሔር በማቅረብ ተነሳሒው እንደገና ላለመበደል መወሰን ይኖርበታል፡፡ ውሳኔውንም ለመፈጸም የሚያስችለውን የመንፈስ ቅዱስን ረድኤት ለማግኘት ተነሳሒው ሁልጊዜ ተግቶ መጸለይ አለበት፡፡

## ኑዛዜ

ከዚህ ቀጥሎ ተነሳሒው ኃጢአቱን ሥልጣነ ክህነት ላለው ካህን ይናዘዛል፡፡ ኑዛዜ ማድረግ በቅዱሳት መጻሕፍት የታዘዘ ነው፡፡ “ከነዚህም ነገሮች በአንዲቱ በደለኛ ሲሆን፥ የሠራውን ኃጢአት ይናዘዛል፡፡ ስለ ሠራው ኃጢአት ለእግዚአብሔር የበደል መሥዋዕት ያመጣል፤. . . ካህኑም ስለ ኃጢአቱ ያስተሠርይለታል፡፡ . . . እርሱም ይቅር ይባላል” (ዘሌ.5፥5-6 እና 10)፡፡ ከዚህ ጥቅስ የኃጢአት ሥርየት ለማግኘት ለካህን መናዘዝ እንደሚገባን እንማራለን፡፡ ስለዚህ ኃጢአታችንን ለአናዛዡ ካህን ከበደሉ ዓይነትና ሁኔታ ጋር መናገርና ማስረዳት ይገባል፡፡ ስንናዘዝም ከእንባና ከፀፀት ጋር ሆነን ከካህኑ ጋር እግዚአብሔር አብሮ እንደሚሰማን አምነን በእውነት መናገር ያስፈልጋል፡፡ በሽታውን የሰወረ መድኃኒት አያገኝም ተብሏልና ለነፍስ ቁስል ሐኪም ለሆነው ለካህኑ ኃጢአታችንን ከሰወርን ለነፍስ የሚሆነውን ፈውስ ለማግኘት አንችልም፡፡

“ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል” ተብሎ ተጽፏልና (ምሳ.28፥13)፡፡ የጌታ ወንድም ያዕቆብ የተባለውም ይኸንኑ ያስተምረናል፡፡ “እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፥ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች” (ያዕ. 5፥16)፡፡

እርስ በእርሳችን በቂም በቀል ሳንያያዝ የበደልነውን እየካሥን፥ የበደለንንም ይቅር እያልን ብንናዘዝና የሰማዩ አባታችንንም በጸሎት ብንጠይቀው ምሕረትንና ፈውስን ይሰጠናል፡፡ ነገር ግን እኛ ማንንም አልበደልንም፥ ኃጢአትም የለብንም ብንል እግዚአብሔርን ሐሰተኛ ማድረጋችን ስለሆነ እንጠንቀቅ፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ እንዳለው፡- “ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም፡፡ በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው፡፡ ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም” (1ኛዮሐ.1፥8-10)፡፡

## ፍትሐትና ቀኖና

እንግዲህ ተነሳሒው በእውነት ኃጢአቱን አውቆ ለካህኑና በስውርም ለሚያየውና ለሚሰማው ለእግዚአብሔር ከተናዘዘ በኋላ ከካህኑ ሁለት ነገሮችን ይቀበላል፡፡ እነርሱም ፍትሐትና ቀኖና ናቸው፡፡ ፍትሐት ማለት ከኃጢአት እሥራት የሚፈታበት ነው፡፡ ቀኖና ማለት ለኃጢአቱ ምክርና ተግሣፅ የሚያገኝበትን፥ የንስሐ ቅጣት የሚቀበልበትን፥ ካሣ (መቀጮ) የሚከፍልበትን ሁኔታ

የሚያመለክት ነው፡፡ ፍትሐት የሚሰጠው ካህኑ የንስሐውን የጸሎት ሥነ ሥርዓት ከፈጸመ በኋላ "እግዚአብሔር ይፍታ" ሲል ተናዛዡ ወይም ተነሳሒው ከኃጢአቱ እሥራት ይፈታል፥ ከእግዚአብሔርም ይቅርታን ያገኛል፡፡ ንስሐ የገባው ሰው ከኃጢአቱ ተፈትቶ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቁ ታላቅ ጸጋ ነው፡፡

ለኃጢአታችን ሥርየት እንደዚህ ዓይነቱን ቀላል መንገድ ስላዘጋጀልን ክርስቶስን ማመስገን ይገባናል፡፡ ብዙ ሳንደክም ወንድማችንና አባታችን ለሆነው ካህን በመናዘዝና ምክሩንና ቀኖናውን በመቀበል በኃጢአት ከሚመጣብን የዘላለም ቅጣት መዳናችን እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው፡፡ ይህንንም ሥልጣን ለካህናት የሰጣቸው እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ከላይ ተገልጿል፡፡ እንግዲህ ፍትሐት የተቀበለ ተነሳሒ ሁሉ ኃጢአቱ በሙሉ የተሠረየለት ስለሆነ ከዘላለም የሞት ቅጣት ነፃ ይሆናል፡፡

ምንም እንኳ ተነሳሒው ከዘላለም የሞት ቅጣት ቢድን፥ ዓይነቱና መጠኑ የተለያየ ጊዜያዊ ቅጣት መቀበል ይገባዋል፡፡ ይህም የንስሐ ቀኖና ይባላል፡፡ ጊዜያዊ ቅጣት ወይም ቀኖና ያስፈለገበት ምክንያት ኃጢአት መሥራት ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ ለተነሳሒው ለማሳሰብና ዳግመኛ እንዳይበድል ለማስጠንቀቅ እንዲሁም ደግሞ ሥጋን በመገሠጽ ለነፍሱ የጽድቅንና የደኅንነትን ጉዳና ለማስተማር ነው፡፡

ምንጊዜም ፍቅሩና ምሕረቱ ከእኛ ጋር ቢሆንም እግዚአብሔር በአባትነቱ ባጠፋነው ጥፋት በጊዜያዊ ቅጣት ይቀጣናል፡፡ መልካም አባት ልጁን እንደሚገሥፅና እንደሚቀጣ ዓይነት ይቀጣናል (ዕብራ.12፥5-11)፡፡ እንግዲህ ያልተገራ ልቡና ካለን ለእግዚአብሔር በማስገዛት የኃጢአታችንንም ቅጣት በደስታ በመቀበል የበለጠ ጸጋና ረድኤትን እናገኛለን፡፡ "በዚያን ጊዜ ያልተገረዘው ልባቸው ቢዋረድ፥ የኃጢአታቸውንም ቅጣት ቢቀበሉ፥ እኔ ለያዕቆብ የማልሁትን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ . . . ምድሪቱንም አስባለሁ" ተብሎ ተጽፏልና (ዘሌዋ.26፥41-42)፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በዝሙት የተከሰሰውን የቆሮንቶስን ሰው በሥጋው እንዲቀጣ ፈርዶበታል፡፡ "እንደዚህ በሠራው ላይ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሁን ፈርጀበታለሁ፤ . . . መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው" (1ኛቆሮ.5፥1-5)፡፡ ይኸው ሐዋርያ ለሁለተኛ ጊዜ በጻፈው መልእክቱ ከላይ የተጠቀሰው የቆሮንቶስ ሰው ቅጣቱ የሚበቃው ስለሆነ ማኅበረ ክርስቲያኑ ይቅርታ እንዲያደርግለት ጠይቋል፡፡

"እንደዚህ ላለ ሰው ይህ ከእናንተ የምትበዙት የቀጣችሁት ቅጣት ይበቃዋልና እንደዚህ ያለው ከልክ በሚበዛ ኀዘን እንዳይዋጥ፥ ይልቅ ተመልሳችሁ ይቅር ማለትና ማጽናናት ይገባችኋል፡፡ ስለዚህ ከእርሱ ጋር ፍቅርን እንድታጸኑ እለምናችኋለሁ፤ ስለዚህ ደግሞ ጽፌ ነበርና፤ . . ." (2ኛቆሮ.2፥6-11)፡፡ እንግዲህ የሐዋርያውን ምክር ሰምተን፥ ዛሬ የምንገኘው ክርስቲያኖችም በበደላችን ምክንያት ካህኑ የሚሰጠንን ምክርና ተግሣፅ አዳምጠን የንስሐውንም ቅጣት ማለት ቀኖናውን ተቀብለን በደስታ ብንፈጽመው መንፈሳዊ ደኅንነታችን ይጠበቃል፤ መንፈሳዊ ግዴታችንንም እንወጣለን፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ቀኖና የሚሰጠው እንደ ተነሳሒው የኃጢአት ዓይነትና ሁኔታ ታይቶ ነው፡፡ ካህኑ የተነሳሒውን የኑሮ ሁኔታና ያጋጠመውንም ፈተና በማስመልከት ምክርና ትምህርት ይሰጠዋል፡፡ እንደ መልካም የነፍስ ሐኪም እንደ በሽታው ሁኔታ፥ ካህኑ አስፈላጊውን መንፈሳዊ መድኃኒት ይሰጣል፡፡ የቀኖና አሰጣጥ መንገዱና ዓይነቱ ብዙ ነው፡፡ ለአንዳንዱ ተነሳሒ የቃል ምክርና ተግሣፅ ብቻ የሚበቃው አለ፡፡ ለሌላው ጾም ብቻ ወይም ከስግደት ጋር ቀኖና ይሰጠዋል፡፡ ልዩ የንስሐ ጸሎት፥ ምጽዋት፥ ለተበደለው

www.eotc-mkidusan.org

ወገን ካሣ መክፈል፥ ለችግረኞች አገልግሎት መስጠት፥ አስፈላጊም ከሆነ ለተወሰነ ጊዜ ከቁርባን መለየት ወይም ልዩ ልዩ አስቸጋሪ ነገሮችን መፈጸም ወይም ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ኑሮ የሚጠቅሙ የጉልበትም ሆነ የአእምሮ ሥራ መሥራትና የመሳሰሉት ሁሉ ከቀኖና ውስጥ ይቆጠራሉ።

እንግዲህ የሚሰጠንን ቀኖና ያለ ቅሬታ በደስታ ተቀብለን ብንፈጽመው ለነፍሳችንም ለሥጋችንም የሚጠቅም ጸጋና በረከትን እናገኛለን። እንዲያውም "ሞት የማይገባውን ኃጢአት" ያደረጉትን ዘመዶቻችንና ባልንጀሮቻችንን ሁሉ እያሰብን፥ በጸሎትም እየማለድን፥ እነርሱንም ንስሐ እንዲገቡ እየመከርን፥ በገዛ ፈቃዳችን ካህኑ ለራሳችን ከሰጠን ቀኖና በመጨመር ብንፈጽመው በኃጢአት ለተጐዱት እኅቶችና ወንድሞች የእግዚአብሔርን ምሕረት እንደሚያስገኝላቸው አያጠራጥርም። እንደዚህ አድርጐ ስለ ባልንጀራው ደኅንነት እግዚአብሔርን ለሚለምን ሰው ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ እንዳለው "ሞትም የማይገባውን ኃጢአት ላደረጉት ሕይወት ይሰጥለታል" (1ኛዮሐ.5፥16)።

## የንስሐ ጸጋ

እንግዲህ ቀላል መስሎ በሚታየው የምሥጢረ ንስሐ ሥርዓት ማለት በሚፈጸመው ጸሎት፥ በሚደረገው የልብ ኀዘንና እንባ፥ በሚሰማው ኑዛዜ፥ ካህኑ በሚሰጠው ፍትሐትና ቀኖና አማካኝነት ከፍተኛ ጥቅም ያለውን የማይታየውን የእግዚአብሔርን ጸጋ እናገኛለን። ከሰውና ከእግዚአብሔር ተጣልቶ ከመኖርና ከዘላለም ቅጣት እንድናለን። የኃጢአት ሥርየትንና ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅን እናገኛለን። በውኑ ሰው ከፈጣሪው ጋር ከመታረቅ የበለጠ ምን ነገር አለ? ለሰው የሚጠቅሙ ሌሎች ነገሮች ሁሉ ከእርቅ በኋላ የሚገኙ ናቸውና።

ንስሐ መግባት ራሱ እንደ ጸጋ ይቆጠራል። በንስሐ የምንቀበለው ቀኖና ችግር ያለበትም ቢሆን ለሚበልጠው ጸጋ ያበቃናል። በዚህ ዓለም ሳለን የምንቀበለው ትንሹ መከራ ከዘላለም ሥቃይ ያድነናል። ስለዚህ ስለ ንስሐ የምንቀበለውን መከራ እንደ ጸጋ አድርገን በደስታ እንድንቀበለውና ከክርስቶስም ለምናገኘው ለበለጠና ለዘላለማዊ ጸጋ እንድንዘጋጅ ቤተ ክርስቲያን ለተነሳሕያን ልጆቿ ሁሉ መምከርን አታቋርጥም።

ምሥጢረ ንስሐ ስለ ኃጢአታችን መከራን በፈቃዳችን እንድንቀበለው ያስተምረናል። ስለ ኃጢአታችንም ልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራ የተቀበለውን ክርስቶስን ያሳስበናል። ከእርሱም መከራ ጋር እንድንተባበርና በምሥጢረ ጥምቀትም ከሕማሙና ከሞቱ ጋር አንድ መሆናችን የሚነገረው ከኃጢአት መለየታችንን ለማመልከት ነበር። ነገር ግን በኃጢአት በመሰነካከል በጥምቀት ያገኘነውን ጸጋ እንዳናጣ ንስሐ የጥምቀትን ጸጋ ያድስልናል፤ ያጠናክርልናል። በእግዚአብሔር ጸጋ ውስጥ ጸንተን እንድንኖር የሚረዳን በምሥጢረ ንስሐ የምናገኘው ጸጋ ነው።

# 7. ምሥጢረ ቀንዲል

## ትርጉም

ምሥጢረ ቀንዲል ማለት ካህኑ ለታመመው ክርስቲያን በሚያደርገው ጸሎትና በሚሰጠው ቡራኬ በሚቀባውም ቅብዐ ቅዱስ አማካኝነት በእግዚአብሔር ጸጋ የሚገኘውን የሥጋና የነፍስ ፈውስ የሚያመለክት ምሥጢር

www.eotc-mkidusan.org

ነው፡፡ ከሥጋ ፈውስ ጋር የኃጢአት ሥርየትም የሚገኝበት በመሆኑ እጥፍ ድርብ ጸጋን የሚያሰጥ ምሥጢር ነው፡፡ "ቀንዲል" የሚለው ቃል ቀጥተኛ ትርጉሙ "በዘይት የሚበራ መብራት ወይም ማብሪያ" ማለት ሲሆን በመጽሐፈ ቀንዲል መሠረት በታመመው ሰው አጠገብ ሥርዓተ ጸሎቱ ሲፈጸም የሚበራውን መብራት ያመለክታል፡፡

ምሥጢረ ቀንዲል ለሕሙማን ሁሉ አይፈጸምም፡፡ እንደ ምድራዊ የሕክምና ሥራ መታየትም የለበትም፡፡ ለሥጋ ፈውስ ብቻ የሚደረግ የመድኃኒት ዓይነት አድርጐ መገመት አይገባም፡፡ የታመመው ሰው ምሥጢረ ቀንዲል የሚቀበለው የሥጋውን መዳን ብቻ ሳይመለከት የነፍሱን መዳን በማስቀደም ያሰበ እንደሆነ ነው፡፡ ስለዚህ ቀንዲል ከንስሐና ከቅዱስ ቁርባን ጋር አብሮ የሚፈጸም እንጂ በተናጠል ብቻውን መፈጸም እንደሌለበት ምእመናን ሁሉ በቅድሚያ ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በጽኑ ሕመም ተይዞ ሞቱን የሚጠባበቅ ሁሉ የተጠቀሱትን ሦስቱን ማለት የንስሐን፥ የቀንዲልንና የቁርባንን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መፈጸም ይገባዋል፡፡

## የምሥጢረ ቀንዲል አመሠራረት

ይህ ምሥጢር ጌታችን ለሐዋርያት ድውያንንም እንዲፈውሱ፥ሙታንን እንዲያስነሡ፥ ለምጻሞችን እንዲያነጹ፥ አጋንንትን እንዲያስወጡ፥ የሕዝቡንም ኃጢአት እንዲያስተሠርዩ ሥልጣን በሰጣቸው ጊዜ የተመሠረተ መሆኑን እናምናለን (ማቴ.10፥8፤ 18፥18)፡፡ " አሥራ ሁለቱንም ወደ እርሱ ጠራ ሁለት ሁለቱንም ይልካቸው ጀምር፥ በርኵሳን መናፍስትም ላይ ሥልጣን ሰጣቸው፥ . . . ወጥተውም ንስሐ እንዲገቡ ሰበኩ፥ ብዙ አጋንንትንም አወጡ፥ <u>ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሷቸው</u>" (ማር.6፥7 እና 12-13)፡፡ እንግዲህ ከዚህ ጥቅስ የምንማረው ቅብዐ ዘይት እየቀቡ ድውያንን መፈወስ በጌታ ትእዛዝ በሐዋርያት የተጀመረ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህም ምሥጢረ ቀንዲል ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እንደ አንዱ ተቆጥሯል፡፡

ምሥጢረ ቀንዲል እንደ አንድ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ምሥጢር የተቆጠረበት ምክንያት ከሥጋ ፈውስ ጋር የነፍስም ጤንነት ማለት ከኃጢአት ደዌ የመፈወስም ኃይል ስላለው እንደሆነ ከላይ አመልክተናል፡፡ ይኸንንም ከያዕቆብ መልእክት ለመገንዘብ እንችላለን፡፡ "ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ቀሳውስት ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት፡፡ የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደሆነ ይሠረይለታል" (ያዕ.5፥14-15)፡፡ ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ይህን ሥርዓት በመከተል ካህኑ የታመሙትን ምእመናን በመጠየቅ፥ ሥርዓተ ጸሎቱን በማድረስና ቅብዐ ቅዱስን በመቀባት ከሥጋ ደዌያቸው እንዲፈወሱ እግዚአብሔርን ይለምናል፥ ኃጢአታቸውንም ያስተሠርይላቸዋል፡፡

## ለነፍስና ለሥጋ ስለሚሰጠው የፈውስ ጸጋ ግንኙነት

እንደ ሌሎቹ ምሥጢራት፥ ምሥጢረ ቀንዲልም በሚታይ አፈጻጸም ወይም ሥርዓት የማይታየውን ጸጋ ያስገኛል፡፡ ቀላል መስሎ በሚታየው ቅብዐ ቅዱስ፥ በካህኑም ሥርዓተ ጸሎት የማይታየው የነፍስና የሥጋ ፈውስ ይሰጣል፡፡ ይህም ሊገኝ የሚችለው የታመመው ሰውና ቤተሰቦቹ በንስሐና በእምነት ተዘጋጅተው ከእግዚአብሔር ምሕረትን ደጅ እየጠኑ በመጠባበቅና ክርስቲያናዊ ግዴታቸውን በመፈጸም ነው፡፡ ምክንያቱም ሥጋና ነፍስን የፈጠረ፥ መዳንንም

www.eotc-mkidusan.org

የሚሰጥ እርሱ ፈጣሪያችን የሕመምተኛውን የሥጋ ፈውስ ብቻ ሳይሆን የቤተ ሰቡን ሁሉ የነፍስ መዳን ስለሚፈልግ ነው፡፡ እርሱ ሲፈቅድ በሽታው በሙሉ ሊድን ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜም የማይድንበት ምክንያት አለው፡፡ እንዲህም የሚሆነው እግዚአብሔር ባወቀ የታመመውን ሰው ለመጉዳት ሳይሆን በነፍሱ የሚድንበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር የሁላችንም አባት ነው፡፡ ያጠፉትንም ልጆች ይገሥፃል፡፡ እርሱ ባወቀ የነፍስን ኃጢአት በሥጋ ላይ በሽታን ወይም ሌላን መከራ በማምጣት ይቀጣናል፡፡ በስውር የሚያየን እግዚአብሔር አባታችን የነፍስ አባታችንና አምላካችን ስለሆነ ሰው በማያውቀው ምሥጢር የንስሐ ቀኖና ይሰጠናል፡፡ እስክንጨርስም ይጠብቀናል፡፡ ጊዜው ሲደርስ፥ ፈቃዱም ሲሆን ይፈውሰናል፡፡

እርሱ ባለቤቱ የነፍሳችንን ደኅንነት ከሥጋችን ይልቅ አብልጦ ስለሚያስብ ስለ ሥጋችን መታመም እምብዛም መጨነቅ አያስፈልግም፡፡ "<u>በሥጋ መከራን የተቀበለ ኃጢአትን ትቷልና</u>" (1ኛጴጥ.4፥2) በማለት ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዳስተማረን ከኃጢአት በሽታ የምንላቀቅበትን በመጀመሪያ ማሰብ ይኖርብናል፡፡ የነፍሳችንን ጤንነትና ደኅንነት ካገኘን በኋላ ሌላው በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ይሆናል፡፡ የሥጋ መከራ ለነፍሳችን የሚጠቅመው፥ መከራን እንደ ጸጋ ቆጥረን ለነፍሳችን የሚያስፈልገውን መልካም ነገር ሁሉ በመፈጸም እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

እንግዲህ በደዌ ዳኝነት በአልጋ ቁራኝነት የምንገኝ ሕሙማን ሁሉ በሁኔታችን ተስፋ ሳንቆርጥ መከራውን በትዕግሥትና በአኰቴት መቀበል አለብን፡፡ እንዲያውም በመጠኑም ቢሆን የኢዮብ ጸጋና በረከት ተካፋዮች በመሆናችን ደስ ሊለን ይገባል፡፡ የንስሐ አባታችንንም በመጥራትና ጸሎተ ቀንዲልም እንዲያደርሱልን መዘጋጀትና ኃጢአታችንንም መናዘዝ ከኃጢአት ደዌ ያድነናል፡፡ በካህኑ ጸሎትና መንፈሳዊ ምክር ሕመምተኛው የመንፈስ እርካታን በማግኘት የሥጋ ሕመሙም እየቀለለት ሊሄድ ይችላል፡፡

መቼም ሰው እግዚአብሔርን የሚያስበውና ዕለተ ሞቱን የሚያስታውሰው መከራ ሲገጥመው ወይም በበሽታ ሲያዝ ስለሆነ ይህንን አጋጣሚ ለነፍሳችን ጥቅም እንድናውለው በጥበበ እግዚአብሔር የተዘጋጀ እንደሆነ እናስተውላለን፡፡ በዚህን ጊዜ የሞት ፍርሃትና የሐሳብ ሁከት ሲያጋጥመን ስለ ነፍሳችን ደኅንነት ማሰብ እንጀምራለን፡፡ ስለዚህ ሕሙማን ሁሉ ምሥጢረ ቀንዲልን እየፈጸሙና ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ ሥጋውና ደሙን ተቀብለው ቢጠብቁት የእግዚአብሔርን ጸጋና ምሕረት ያገኛሉ፡፡

ምሥጢረ ቀንዲል የሥጋ ፈውስ መስጠት አለ መስጠቱ ሳይሆን ቁም ነገሩ ሕመምተኛው ያጋጠመውን ሕመም በአኰቴት እንዲቀበለውና ከነፍስ ሕመምና ሞት እንዲድን ማድረጉ ነው፡፡ የሥጋ ሞትም ቢመጣ በነፍስ ሕያው ሆኖ ከክርስቶስ ጋር ያለ መከራና ሕመም መኖር እንደሚቻል የሚያስገነዝብ የተስፋ ጸጋ ከዚሁ ምሥጢር ይገኛል፡፡ ሕመሙንና መከራውን ከክርስቶስ ሕማምና ሞት ጋር በማስተባበር ሕመምተኛው ከጌታ ጋር ያለውን አንድነት ይገልጻል፡፡ ይህንንም በፈቃደኝነት ሲያደርገው ታላቅ መጽናናትን ከመንፈስ ቅዱስ ያገኛል፡፡ እስከ መጨረሻውም በመታገሡና እስከ ሞትም በፈጣሪው በመተማመኑ የሕይወት አክሊልን ይቀዳጃል፡፡

www.eotc-mkidusan.org

በዚሁ ጽሑፋችንን እናጠቃልላለን፡፡ በመጨረሻም ስሙን ያልገለጸው የመዝገበ ሃይማኖት ደራሲ በመጽሐፉ ፍጻሜ የጻፈውን በመጥቀስ የሚከተለውን ስብሐተ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በመሆን እናቀርባለን፡፡

**"ስብሐት ለእግዚአብሔር ወጣኒ ወፈጻሚ ከሃሊ ወገባሬ ኵሉ ሎቱ ይደሉ አኰቴት እስከ ዘመነ ዘመናት በምድር ወበ ሰማያት በባሕር ወበቀላያት ለዓለመ ዓለም አሜን፥**

**ለሚችል ለሚጀምር ለሚፈጽም ቻይ ሁሉን ለፈጠረ እግዚአ ብሔር ምስጋና ይድረሰው ለእሱ ከዘመን እስከ ዘመናት በምድርም በሰማይም በባሕርም በጥልቆችም ለዘለዓለሙ ምስጋና ይገባዋል አሜን፡፡"**

"እመሂ ስሕትኩ አንትሙ አለ በመንፈስ አርትዕዎ፥ የተሳሳትኩትም ቢኖር እናንተ በመንፈስ ያላችሁ አቃኑት" [102]

እነሣሥቶ ላስጀመረን፥ አስጀምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን፤ ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን፡፡ [103]

---

[102] መዝገበ ሃይማኖት፤ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የድርሰት ክፍል ተዘጋጀ (1959 ዓ. ም.) ገጽ 111፡፡

[103] "እግዚኦ ረስየነ ድልዋነ ከመ ንበል በአኰቴት አቡነ ዘበሰማያት"

www.eotc-mkidusan.org